# ነፃነቴን እንደገና ተቀዳጀሁ!!

## ከጀርመን ወደ ኢትዮጵያ ደርሶ መልስ

ይህች አጭር ጽሁፍ ከዘመዴ ከወይዘሮ ዘነበች ጋር ኢትዮጵያ ስድስት ሳምንት ቆይታ ከተመለሰች በኋላ የተደረገ ውይይትና ቃለ-ምልልስ ነው። ዘነበች ኢትዮጵያ በቆየችባቸው ስድስት ሳምንታት ተቀምጠን በሰፊው እንድታወጋኝና ፣ የውይይታችንና የቃል ምልልሳችንም ውጤት በመጽሄት ላይ ወይም በኢትዮጵያውያን ዌብ ሳይት ላይ እንዲወጣ ማሳመን ነበረብኝ። ለሰፊ ውይይት ጊዜ እንደሌላትና እንደዚሁ ዐይነት ውይይት ብዙ ነገሮችን እንደሚያስታውሳትና ወደ ሀዘንም እንደሚከታት ስለተገነዘበች ማውጣትና ማውረድ ነበረባት። ከረጅም ውይይትና ማሳመን በኋላ የደረስንበት ስምምነት ቃለ-መጠይቅ ብቻ መሆኑ ቀርቶ የሃሳብ ልውውጥም እንዲታከልበት አስተሳሰባችንን ሰፋ በማድረግ እሷም እኔን እንድትጠይቅ በመስማማት ለሰፊው ኢትዮጵያዊ የሚዳረስ ብዙ መልዕክቶችንም የሚያካትት ጽሁፍ ሆኖ እንዲወጣ ተስማማን።

ዘነበች የፖለቲካ ሰው አይደለችም። በተለይ ስለ ኢትዮጵያ ፖለቲካ ሲነሳባት ያንገሸግሻታል። ኢትዮጵያዊ ሆኜ ባልተፈጠርኩ ኑሮ እያለች አንዳንድ ጊዜ ብስጭት ስትል ምሬቷን ትግልጻለች። ለምንድን ነው እንደዚህ ዐይነት ማጥ ውስጥ ገብተን እርስ በራሳችን እየተነካከስን የምንኖረው ? ምንስ ነገር ነው ለልጆቻችንና ለልጅ ልጆቻችን ጥለንስ የምናልፈው ? ብላ ምርር እያለች አንዳን ድ ገዜ ታለቅሳለች። ስለዚህም ፖለቲካ ሲነሳባት ያንገሸግሻታል ፤ የሰው ልጅ ካለፖለቲካ ፣ በተለይም እኛ ኢትዮጵያውያኖች ካላፖለቲካ መኖር አንችልም ወይ እያለች ስሜታዊ ንግግር ትሰነዝራለች። በፖለቲካና በሌሎች ህብረተሰብአዊ ግኑኝነቶች መሀከል ያሉትን መተሳሰሮች በፍጹም ልትረዳ አትችልም።

ዘነበች በአለፉት አስራ ስድስት የኢህአዲግ አገዛዝ ዘመን ወደ ኢትዮጵያ ከአምስት ጊዜ በላይ ተመላልሳለች። ያረጁ እናት ስላሏት እሳችውን እየተመላለሱ ማየት ትልቅ የመንፈስ ደስታ እን ደሚሰጣት ትነግረኛለች። በተለይም በአብዮቱ የተነሳ በቤተሰቦቿ ላይ በልጅነቷ ብዙ ነገር ስለደረሰ ያንን አገር ማየት አትፈልግም። የናት ነገር ሆኖባት እረፍት ማግኘት አልቻለችም። ፈረንጅ አገር እየቆየች በሄደች ቁጥር ስለ አገሯ ያላት አስተሳሰብ ግን እየተቀየረ እንደመጣ አልፎ አልፎ ታጫውተኛለች። በተለይም የመጨረሻዎቹ ሁለት ጉዞዎቿ ምንም ደስ እንዳላላትና ፣ አገሪቱም እያደገች ከመሄድ ይልቅ እየቀጨጨችና እየደኸየች በመምጣቷ ያለመደሰቷን ፣ በተለይም ይህ የመጨረሻው ጉዞዋ እንዳስመረራትና በሁሉም አኳያ ነፃነት የሌለባት አገር ሆኖ ነው የተሰማት። ስለዚህም ጀርመን ስትመለስ "ነፃነቴን እንደ ገና ተቀዳጀሁ" ብላ አወራችኝ። ውይይታችንም በዚህ እንዲቀጥልና ነፃነቴን እንደ ገና ተመልሼ ተቀዳጀሁ ስትል ምን ማለቷ እንደሆነ በሰፊው እን ድታብራራልኝ ወደ ሰፊው ውይይታችን አመራን።

**ፈቃዱ** ፣ ዘነበች የዘንድሮውን ጉዞሽን እንዴት አገኘሽው ? በየትኛውስ የአየር መንገድ ነው የሄድሽው ?

**ዘነበች** ፣ በአለፉት አራት ጉዞዬ በኢትዮጵያ አየር መንገድ ነበር የተጓዝኩት። ከአንዴም ሁለቴም ደስ የማይሉ ነገሮች ስላጋጠሙኝ ፤ ከዚያን ጊዜ ወዲህ በኢትዮጵያ አየር መንገድ መጓዜን አቁሜያለሁ። በኢትዮጵያ አየር መንገድ ላለመሄድ ምዬአለሀ ፣ ተገዝቼአለሁ!! በቱርክ አየር መንገድ ነው የተጓዝኩት።

**ፈቃዱ** ፣ ለመሆኑ እንደዚህ የሚያስመርር ምን ነገር አጋጠመሽ ? ምክንያቱን ዘርዘር አድርገሽ ልታስረጂኝ ትቺያለሽ ?

**ዘነበች** ፤ እንደምታውቀው የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከፍራንክፈርት በፈረንጅ አቆጣጠር

ከምሽቱ 23:30 ሲሆን ነው የሚነሳው። እንዳጋጣሚ ሆኖ ደጋግሜ በሄድኩበት ጊዜ አብዛኛው ተሳፈሪ ሀበሻ ነበር። አንድ ሰሞን አውሮፕላኑ አስመራም ያርፍ ስለነበር ብዙ ኤርትራውያንም ነበሩ አብረውን የተጓዙት። ካለወትሮው የተሳፈርን በት አውሮፕላን ትንንሽና ተዝናንተህ ልትቀመጥበት የምትችል መቀመጫዎች አልነበሩትም። በዚህ ላይ ሁለቱን ልጆቼን ይዤ ነበር የተጓዝኩት። ይህ አይግረምሽ ብለው የማይሆን እራት ያቀርቡልናል። የታሸገና የምጠላው የጀርመን ምግብ ቀረበልን። በዚህ ላይ መስተንግዶው ጥሩ አልነበረም። እንደምንም አዲሰ አበባ ደረሰን። ስመለስ ግን የመጣሁበት አውሮፕላን ዘመናዊና ትልቅ ነበር። ፈረሰ የሚያስጋልብ ሜዳ ያህል አለው። በዚህ ላይ ትልቅ ቴሌቬዥን አለው። ወዲህ ወዲያ ዞር ብዬ ስመለከት 90% የሚሆነው ተሳፋሪ ፈረንጅ ነበር። የቀረበልንም ምግብ ሆነ መጠጥ ለየት ያለ ነበር።ስንሄድ ቢራ እንኳ ያልቀረበውን ያህል ሻምፓኝና ኮኛክ ነበር የምንጠየቀው። ልዩነቱ ያኔውኑ ሊገባኝ አልቻለም። ሁለተኛና ሶስተኛ ጊዜ ስመላለስ እንደዚህ ዐይነት መሰተናግዶ ያጋጥመኛል። አውሮፕላን ጣቢያም ስደርስ በፈረንጅና በኛ መሀከል የነበረውን ያቀባበል ልዩነት የኋላ ኋላ እየተገነዘብኩ መጣሁ። አሁን ዘረኝነት እንዳለበት ተገነዘብኩ። ጀርመን አገር ለረጅም ዐመታት ስኖር ያላጋጠመኝን ዘረኝነት በግልጽ በኢትዮጵያውን ዘንድ ተመለከትኩ አለችኝ።

__ፈቃዱ__ ፣ ይህ ያለመማርና ያለማወቅ ጉዳይ ነው። ትንሽ ዕውቀት አደገኛ ነው ብያት የኔን ልምድ ደግሞ ዘረዘርኩላት።ይኸውልሽ እኔም የዛሬ አስራ አራት ዐመት ወደ ኢትዮጵያ ስጓዝ ልክ እንደዚህ ዐይነት ነገር አጋጥሞኛል። እንደዚሁ ተጨናንቀን ነበር የሄድነው። ስንመለስ የአውሮፕላኑ ስፋትም ሆነ መስተንግዶው ልዩ ነበር። በዚያ ላይ ደግሞ ቴሌቪዥኑ ሌላ ነበር። ፈረንጅ እንደዚሁ ጥቅ ብሎ ነበር አብሮን የተጓዘው። አንድ አስር ያህል ኢትዮጵያውያን ወደ አሜሪካ የሚጓዙ ነበሩ። በእድሜ ገፋ ያሉ ። እንደሚመስለኝ የአየር መንገዱ ሰራተኞች። ታዲያ የሆሊ ወድ ፊልም አይናቸውን አፍጠው ይመለከታሉ። ትዝ ያለኝ ያኔውኑ የአሜሪካ ባህል በሽማግሌው ጭንቅላት ውስጥ ሰርጎ እንዴት እንደገባ ነው። እኔ ደግሞ ጥሎብኝ የተመረጠ ፊልም ካልሆነ ብዙም የሆሊ ውድ ፊልም መመልከት አልወድም። ብዙ ጊዜ ደስ የሚለኝ የቼኮዝለቫኪያ የቤተሰብ ወይም ዶከሜንተሪ ፊልሞች ናቸው ብዬ ሳሰረዳት ፣ አዲሰ አበባ አውሮፕላን ጣቢያ አርፈን እቃችንን ስንጠብቅ ያጋጠመኝን ነገርኳት። የዚያን ጊዜ የስድስት ዐመት የምትሆነውን ሴት ልጄን ይዤ ሄጄ ስለነበር መጸዳዳት ስለፈለገች ጓደኛዬ ይዟት ወደ መጸዳጃው ቦታ ገባ። ያኔውኑ ስታየው እየጮኸች ወጣች። ምነው ብላት እንደዚህ ዐይነት ቦታ አልቀመጥም ፤ በጣም ቆሻሻ ነው እያለች መለሰችልኝ ብዬ ልምዴን ነገርኳት።

__ዘነበች__ ፣ የኛ ነገር ምኑ ተይዞ ምኑ ያልቃል ብለህ ነው። ከዐመት ዐመት ይሻላል ስል በሄድኩ ቁጥር እዚህና እዚያ ትላለቅና ዕቅድ የሌለው ቤት ከመሰራቱ በስተቀር አገሪቱ ወደ ኋላ የምትጓዝ ነው የምትመስለው። እዚህና እዚያ እንስሳ ለማደን እን ደሚያደባ ሰው ወታደር የሚመስሉ ሽጉጥና ጠብመንጃ ይዘው ከማየት በስተቀር አገሪቱን በስነስርዓት የሚያስተዳድራት ሰው ያለ አይመስለኝም። ባለስልጣናቱም እዚህ አገር እንደምናየው ስለ አገሪቱ የፖለቲካ ፣ የኢኮኖሚ ፣ የህብረተሰብአዊና የጤና መስክ ጉዳይ በየጊዜው ጋዜጣዊ መግለጫ ሲሰጡ ወይም ደግሞ በቴሌቪዥን ውይይት ሲካሄድ አይታይም። ህዝቡም ኑሮ የሰለቸውና አገር ጥሎ ለመጥፋት የተነሳ ነው የሚመስለው እንጂ በተስፋ አንድ የሚጠበቀው ነገር እንደሌለ ከበፊቱ ማንበብ ይቻላል። ሁሉም አሜሪካ ለመሄድ የሚያሰፈሰፍ ነው የሚመስለው። ሽማግሌው ፣ አሮጌቱ ሁሉ አሜሪካንን ነው የሚናፍቀው። ድሮ እናቶቻችን እየሩሳሌምን ሳታሳየኝ አትግደለኝ ነበር የሚሉት። የዛሬው ዘመን ሽማግሌ አሜሪካንን ሳታሳየኝ አትግደለኝ የሚል ነው የሚመስለው።

__ፈቃዱ__ ፣ ለመሆኑ ሰው እንዴት ይኖራል ? ምንስ ይበላል ?

**ዘነበች** ፣ የሚገርመኝ ነገር አሱ ነው። በተለይ ቀን ከህዝቡ ብዛት የተነሳ መለወሻ በማጣት እየተሸለኮለክ ነው መሄድ ያለብህ። ያ እንደዚያ ከተማይቱን የሞላ ህዝብ ሲመሽ ወዴት እንደሚሄድ ፣ የትስ እንደሚያድር ነው ግራ የሚገባኝ። በጣም ግርም ይለኛል። ያች አገር በሃያ ዐመት ውሰጥ እንደዚህ ዐይነት ለውጥ በማየቷ ፣ በተለይም ደግሞ አዲስ አበባ መጨናነቋ በጣም ያሰፈራኛል። ከተማይቱ በህዝብ ብዛት እየጠበበች ከመምጣቷ ባሻግር በጣም እየሰፋችና ከደብረዘይትና ከሌሎች አቃራቢ ትናንሽ ከተማዎች ጋር እየገጠመች ነው። ሳይታወቅ ግን እዚህ ላይ የኦሮሞ ኤሊቶች ህልም የተዳፈነ ነው የሚመስለኝ። ፊንፍኔ የሚባል ነገር የለም። አንደኛ ፣ ህዝቡ ከዚህም ከዚያም እየፈለሰ በመምጣቱ የተለያዩ ጎሳዎች መኖሪያ ሆናለች። ሁለተኛ ከሌሎች ከተሞች ጋር እየገጠመች በመምጣቷ የፍንፍኔን ካርታ እንዳለ ተቀይሯል። በዚህም የኦሮሞ ኤሊቶች ህልም ተዳፈነ ማለት ነው።ከዚህ ስትነሳ ከህዝቡ ፊት የምታነበው እዚህ አንዳንድ ቅዠታሞች እንደሚሉት ሳይሆን አንድ ህዝብ መሆኑን ነው የሚያረጋግጥልህ። ፈቃዱ ፣ ከሁሉ ነገር ይህ ነው ደስ የሚለኝ። በተረፈ ግን የህዝቡን ኑሮ ስታዬው አንዳንድ ጊዜ መፈጠርህን ያስጠላሃል። ድሮ ከአንዴም ሁለቴም ስመላለስ ይህ ሁሉ ነገር ግልጽ አልነበረልኝም። ፈረንጅ አገር መቆየት ጥሩ ነው መሰለኝ። ከሃያ ዐመት ቆይታ በኋላ ትንሽ ትንሽ ነገሮችን እየተረዳሁ መምጣት ችያለሁ። በኛ ኢትዮጵያውያንና- በጠቅላላው በአፍሪቃ ምድር እንደዚህ ይመስለኛል- በፈረንጆች መሀከል ያለው ልዩነት የሰማይና የመሬትን ያህል ርቀት ያለ ነው የሚመስለኝ። አንዳንድ ጊዜ እራሴን ስጠይቅ ለስራ ወይስ ለጥፋት ነው የተፈጠርን ? ለመሆኑ ማሰብ እንችላለን ወይ እያልኩ እራሴን አንዳንድ ጌዜ እጠይቃለሁ። ድሮ የማያሰጨንቁኝ ነገሮች ሁሉ ያስጨንቁኛል። በጣም ተለውጬአለሁ ይገርምሃል።

**ፈቃዱ** ፣ አየሽ እንደዚህ ነው። በመጠየቅ ብቻ ነው መልስ የሚገኘው። መጽሀፍ ቅዱስ እንኳ አንኳኩ ይከፍትላችኋል ፤ ጠይቁ መልስ ታገኛላችሁ ይላል። ዐይን የሰጠኋችሁ ለማየት ፣ ጭንቅላት የሰጠኋችው ለመመራመር ይላል። እኛ ግን አንዱ ሌላውን ካለጠፋ ሊኖር የማይችል ይመስል ፣ አንዱ ሌላውን እየጠለፈና እያሰናከለ ፣ እየገደለ እያሰረና እያሰቃየ ተግባራችን ሁሉ በዚህ የጥፋት ዙሪያ እየተሽከረከረ እንድንኖር የተረገምን ይመስላል።

**ዘነበች** ፣ በዚህ እንኳ አልስማማህም። ድሮ የኢትዮጵያ ህዝብ ጨዋ ነበር ይባላል። እኔ ትንሽ ልጅ በነበርኩበት ጊዜና አብዮት የምትሉት ፣ እናንተ ያመጣችሁት ጣጣ እስከፈነዳ ድረስ ህዝቡ ተሳስቦና ተጋግዞ ነበር የሚኖረው።

**ፈቃዱ** ፣ ይህንን በሰፊው ወደ ኋላ ላይ እንወያይበታልን ፤ እራሱን የቻለና በቀላል መልስ የማይገኝለት እንዳንቺ ያሉ ብዙም የአብዮቱን ታሪክ ፣ አነሳስና አወዳደቅ ፣ እን ዲሁም የኃይሎችን አሰላለፍ ያላጠኑና ያላጤኑ ብዙ ግራ የተጋቡ ኃይሎች በቀላሉ ሊረዱት የሚችሉት ነገር አይደለም። ለዚህ በቂና ሳይንሳዊ መልስ መስጠት ይቻላል።

**ዘነበች** ፣ አየህ ፈቃዱ እንደዚህ እያላችሁ ነው የምታወናብዱት። ሳይንስ ፣ ቲዎሪ ፣ ዝባዝን ኬ እያላችሁ። በአንድ መንገድ ሲመጠባችሁ በሌላ በር ለማምለጥ ትሞክራላችሁ። ወንጀላችሁን መናገር አትፈልጉም።

**ፈቃዱ** ፣ እኔ ነገሩን ለማስረዳት እችላለሁ አልኩሽ እንጅ ፣ ወንጀል ተሰራ ከተባለ ለወንጀሉ ተጠያቂ አይደለሁም። አብዮቱ ሲፈነዳም ከአንቺ በአንድ ሰባት ዐመት ብበልጥም ነው። ምኑንም የማውቀው ነገር አልነበረም። ክፋቱንም ደጉንም እዚህ መጥቼ የወሬ ወሬ ነው እየሰማሁ የተማርኩትና የኋላ ኋላም የአብዮቱን አዎንታዊና አሉታዊ ጎን የተገነዘብኩት። እየጠለቅሁ ስሄድ ፣ ሳነብና ስመራመር አንዳንዴ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለሁ ይመስለኝ ነበር። ከሩቅ ሆኜ ብዙ ነገሮች ይታዩኝ ጀመር። በዚህም የተነሳ

ቀስ ቀስ እያልኩ ስጽፍ ነገሮች ግልጽ እየሆኑልኝ መጡ። ታሪኩ ባጭሩ እንደዚህ ነው እንጂ በሰው ህይወት ላይ ፈርጀም አላውቅም። ባህርዬም አይፈቅድም። እስቲህ ወደዚህ ጠለቅ ብለን ከመግባታችን በፊት ስለ አየሺው ፣ ስለበላሽውና ስለ ህዝቡ አኗኗር ንገሪኝ። አንባቢውም የድሮውን ታሪክ ለመስማት አይፈልግም።

**ዘነበች** ፣ ጠለቅ ብዬ ስላየሁት ሁኔታ ከመዘርዘሬ በፊት ፣ ጽሁፍህን ሳነብ የተገነዘብኩትና በፍጹም የማይረሳኝ አንድ ነገር አለ። ይኸውም አንዱን ከሌላው መነጠል አይቻልም። አንዱ ከሌላው ጋር የተያያዘ ነው ፣ ስለዚህም የድሮውም በዛሬው ድርጊታችን ላይ ተጽዕኖ አለው እያልክ ለማስተማር ትጥራለህ። አሁን ደግሞ እሱን ሁሉ ረስተህ ሰው ሁሉ የድሮውን ሀተታ ለመስማት አይፈልግም ብለህ አደፋፍነህ ለማለፍ ትሞክራለህ። ሀቀኝነትህን እጠራጠራለሁ።

**ፈቃዱ** ፣ ለመሆኑ ሀቀኛ መሆኔን ትጠራጠሪያለሽ ? ለማለት የፈለግሁት መጀመሪያ ሰው መስማት የሚፈልገው ላይ እናትኩር ነው። የማፍረበትና የምሸፍጥበት አንዳችም ምክንያት የለም። ወንጀል ከሰራሁ ተጠያቂነቴን ማመን የምፈልግ ነኝ። ታሪክን ለመስራት የምታገል ስለሆነ ፣ ታሪክ ለመስራት የሚሻ ሁሉ በተቻለ መጠን ንጹህና ሀቀኛ መሆን አለበት ብዬ ሽንጤን ገትሬ የምታገል ነኝ። አንድ ሰው ከተሳሳተ ወይም ደግሞ ወን ጀል ሰራ ተብሎ የሚታመን ከሆነ ጥፋቱን ማመን አለበት። እኔም ለተቀደሰ ተግባር የቆምኩ ስለሆነ ዋሽቼና በተለይም በአገሬ ላይ ወንጅል ሰርቼ ጥሩ እንቅልፍ ሊወስደኝ በፈጹም አይችልም። የኔ እመቤት ይህ ነው የኔ ዕምነት። እና ወደ ቁም ነገሩ እናምራ ፤ ወደ አየሽው እንግባ።

**ዘነበች** ፣ አየህ ፈቃዱ ሙያዬ ህክምና ስለሆነ በተለይም አንዳንድ ቦታዎችን ከጎበኘሁ በኋላ ብዙ ነገሮች ግልጽ እየሆኑልኝ መጡ። አንደኛ አብዛኛው ህዝብ ገቢ የለውም። ምን ቀምሶ እንደሚውል ፣ ምን በልቶ እንደሚያድር ግራ ይገባኛል። ስራ የለሌው ሰው ገቢ የለውም ማለት ነው። ገቢ ከሌለው ደግሞ አሰፈላጊውን ነገሮች ገዝቶ ሊመገብ አይችልም። ምግብ ካልበላ ደግሞ አቅሙ ደካማ ይሆናል ማለት ነው። አቅሙ ደካማ ከሆነ ደግሞ በቀላሉ ለበሽታ ይጋለጣል ማለት ነው። ይኸ ነው በአገራችን አንደኛውና በቀላሉ መፍትሄ የማይገኝለት። ከዚህ ሌላ ያሉት ሀኪም ቤቶች በየጊዜው በቁጥር እየጨመረ ለሚሄደው የአገራችን ህዝብ ሊዳረሱ አይችሉም። ያሉትም መጣበባቸው ብቻ ሳይሆን በመድሀኒት እጥረት ፣ በመታከሚያ መሳሪያዎች አለመሟላት ፣ ያሉት ደግሞ በንጽህና ስለማይያዙ በሽታ ከአንዱ ታማሚ ወደ ሌላው በቀላሉ ይተላለፋል። የሀኪም ቤቶች አልጋዎች በጣም የተበላሹ ናቸው። እንደደንቡ ከሆነ ሁሉም መቃጠል ያለባቸውና በአዲስ መተካት ያለባቸው ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ ሀኪም ቤቶቹ ከተሰሩ ጀምሮ አንድም ጊዜ አልታደሱም። እንደምታወቀው በአገራችን የማፍረስ እንጂ የማደስ ባህል የለም። ሀኪሞቹ እራሳቸው ባለው ሁኔታ ደንዝዘዋል። ይህንን እንደ ኖርማል ሁኔታ ነው የሚመለከቱት። ማሰብ ያቆሙ ነው የሚመስለው።

**ፈቃዱ** ፣ ባለፉት አስራ አራት ዐመታት የግል ሀኪም ቤቶች በብዛት ተቋቁመዋል። እነሱስ ለህዝቡ የሚሰጡት አገልግሎት ምንድ ነው ?

**ዘነበች** ፣ በርግጥ መዓት የግል ሀኪም ቤቶች እንደ አሸን ፈልቀዋል። ችግሩ ግን እዚያ ሄዶ የሚታከመው ገንዘብ ያለው ብቻ ነው። ሁለተኛ ህጋዊ ቁጥጥርና መለኪያ ስለሌለ ከሚገባው በላይ የመመርመሪያና የህክምና ዋጋ ይጠይቃሉ። በዚህ ላይ መድሀኒቱ ውድ ነው። እነሱም ቢሆኑ ተዓምር ሊፈጥሩ አይችሉም። የአገሪቱ ዕድገት ነጽባራቆች ናቸው። በሙያቸው እጠራጠራለሁ። ምናልባት ታውቅ ይሆናል። እዚህ አገር አንድ ሀኪም በየጊዜው ዕውቀቱን ማደስ(update) አለበት። ልዩ ልዩ የህክምና መጽሄቶችንና መጽሀፎችን ማንበብ አለበት። እነዚህ ደግሞ በአገራችን የሉም።

በቴሌቪዥንና በራዲዮ ስለህክምናና ስለጤንነት በአጠቃላይ ውይይት አይካሄድም። ትምህርት አይሰጥም። ባጭሩ የግል ክሊኒኮች የሚባሉት ገንዘብ ማካበቻ ናቸው እንጂ ብቃትና ጥራት ያለው ህክምና የሚሰጥበት ዘርፍ አይደለም። እንደሰማሁት ከሆነ ብዙ ሀኪሞች ከበሽታው ጋር የማይገናኝ መድሀኒት እየጻፉ ብዙ ሰዎችን ለአደጋ አጋልጠዋል ይባላል። የአገራችን ጉድ ይህ ነው።

ፈቃዱ ፣ ላቋርጥሽና አንድ ከዚህ ጋር የተያያዘ አንድ የጓደኛዬ ጓደኛ የአጫወተኝን ልን ገርሽ። ምስራቅ ጀርመን ውስጥ የስፖርት ህክምና አጥንቶ ከጨረሰ በኋላ ወደ አገሩ ይመለሳል። ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ተቀጥሮ ይሰራ ነበር። ልጁ አልፎ አልፎ የቆዳ በሽታ ስለሚያማት ጥሩ ሀኪም የት እንዳለ ጓደኛውን ጠይቆ ጓደኛው በአገሪቱ ውስጥ ይታወቃል ከሚባለው ሀኪም ጋር ይመራዋል። እንደምታውቂው እኛ አገር ብዙም በቀጠሮ የሚሰራ ነገር ስለሌለ ልጁ ጋር ተነስቶ ይሄዳል። ተመዝግቦ ትንሽ ከጠበቀ በኋላ ከልጁ ጋር ይገባል። ሀኪሙ ቀና ብሎም አላየውም። ከተወሰነ ደቂቃ በኋላ እንደ መዘባነን እያለ እየተንጎራደደ ምን ልርዳህ ብሎ ይጠይቀዋል። እራሱ የህክምና ሙያ ስላጠና ከሀኪመ መልካም አቀባበል ይጠብቅ ነበር። አቀባበሉ ሁሉ ስላናደደው ፣ አን ድ ሀኪም አንድ ሰው ሊታከም በሚሚጣበት ጊዜ እንዴት አድርጎ መቀበልና ፣ ይህ ራሱ በህመምተኛው ላይ አዎንታዊ ተፅዕኖ እንዳለው ያስረዳዋል። ቀጥሎም ፣ ተመልከት አንተ ለምሳሌ ሀኪም ነህ ፤ ሀኪም ቤትህ የሚመስለውን ተመልከት። ደም ሁሉ በየቦታው ተሰራጭቷል። ንጽህና ሳትጠብቅ ፣ መሳሪያዎችህን በየጊዜው ሳታጸዳ እን ዴት አድርገህ በሽተኛ ልታክምና ልትፈውስ ትችላለህ ብሎት በንዴት ጥሎት ይወጣል። መጨረሻ በአገሪቱ የተበላሸ አስታደደር ፣ በቢሮክራሲው ግድ የሌሽነት አገራችን እየወደመች ከማየት ይልቅ ብሎ ባሌቤቱንና ልጆቹን ይዞ ወደ ጀርመን ጓዙን ጠቅልሎ ይመጣል። ከሰውየው ጋር አብረን ተቀምጠን ለጥቂት ስዐታት ያህል አውርተናል። እንዳለኝ ከሆነ በየመስሪያ ቤቱ የተሰገሰገው ፣ ከውሀ ልማት እስከ መብራት ኃይልና ሌላም ቦታ በግድ የለሽነት አገሪቱን ለማውደም የተነሳ ነው የሚመስለው ብሎ ምርር እያለ ነገረኝ።

ዘነበች ፣ አዎ እንደዚህ ጠለቅ ባይል እንኳ የነገሮችን አሰራር እንደዚህ ነው የተመለከትኩት። ሁሉም ተገዶ የሚሰራ የሚመስል እንጂ ሃላፊነት ተሰምቶት በቅልጥፍናና በጥራት የሚሰራ የለም። አብሻቂ ብቻ ነው የተሰበሰበ የሚመስለው። መንግስት ጥፋተኛ ቢሆንም አንዳንድ ሰው እየተነሳ አብሮ አገሪቱን ለማጥፋት የግድ የለሽ ስራ መስራት የለበትም። የኛ ችግር በግለሰቦች ላይ ተንኮል የምንሰራ ነው የሚመስለው። የትውልድ ወንጀል እንደምንፈጽም ፣ አገር እንደምናፈራርስ በፈጹም ግንዛቤ ውስጥ አይገባም። ፈረንጆች ቢንቁን በፍጹም ሊደንቀኝ አይችልም። እራሳችንን ለማሰከበር በጥንቃቄና በቆራጥነት ካልሰራን ዘላለማችንን ለማኝ ሆነን እንቀራለን። እየተናቅን እንኖራለን። ብቻ የአገራችን ችግር ተወርቶ አያልቅም።

ፈቃዱ ፣ እዚህ ላይ አንድ ያነበብኩትን የጥያቄና ምልልስ ልንገርሽ። አቶ ስለሺ ዘፋኙን ወይም በአትዮጵያ አያ ጀምበሬ እየተባለ የሚጠራውን የሰጠውን የጥያቄ መልስ ሳነብ በጣም ነው የአገራችን ሁኔታ ያሳሰበኝ። እንደምታውቂው ውድ ወንድማችን ከተማውን በማጽዳት ፣ አበባ በመትከልና ለህዝብና በተለይ ለወጣቱ ደግሞ ግሩም ባህል እየስታመረው እንደሆነ ይታወቃል። በተለይም በአዲስ አበባ ጥሩ ውጤት እንዳሳየ ሄደው የጎበኙ እንዳሉ ይታወቃል። አቶ ስለሺ ስራውን ለመስራት በማዘጋጃቤትና በየቀበሌው መስሪያ ቤት ሲመላለስ ፣ አንደኛ ፣ ብዙ ጊዜ ይጠብቃል። ሁለተኛ ፣ ለአንድ ጉዳይ በየጊዜው መመላለስ አለበት። ይህ ጉዳይ ክፉኛ ያበሳጨዋል። አንድ ቀን እንደዚሁ ማዘጋጃቤት ሄዶ በራፉ ላይ ሲጠብቅ አን ድም ሰው አይወጣም ፤ አይገባም። ብዙ ሰዓት ይጠብቃል። ግራ ይጋባዋል። ኋላ አንኳኩቶ በሩን ከፍቶ ሲመለከት ሰራተኛው መቀመጫው ላይ ብቻውን ያታሻል። ኋላ ይገባና እዚያው ላይ በቦክስ ይመታዋል። ደብድቦት አንተ በህዝብ የምትቀልድ

ብሎት ጥሎት ይወጣል። እንደዚህ ዐይነት በየቦታው እንዳጋጠመውና በቦክስ እጁ እንዳበጠና እንደተከሰሰም ምን ያህል ሰይጣኖች በየቢሮው እንደተቀመጡና የሰውን እንጀት እንደሚያበሽቁ ከሰጠው መልስ ለመረዳት ችያለሁ። እሱ እንደሚለው ብዙ ሰይጣኖች እንዳሉና ለዕድገትም እንቅፋት እንደሆኑ ነው።

**<u>ዘነበች</u>** ፣ አዎ ብዙ ሰዎች በዚህ ይበሽቃሉ። የውሃ ዋጋ ለመክፈል የውሃ ልማት መስረያ ቤት ቀኑን ሙሉ ውለው የሚመጡ እናቶቻች ቁጥር ትንሽ አይደለም። ገንዘብ እንደዚህ አገር በባንክ እንደልብ የምታስተላልፍበት መንገድ የለም። የአሰራር ሁኔ ታው በጣም የተዝረከረከና ደካማ ነው። እንዴት አዚያ አገር እንደሚኖር አላውቅም። በተለይ ከዚህ ለሄደ።

**<u>ፈቃዱ</u>** ፣ ስለንጽህናውስ የምታወሪኝ ነገር አለ ?

**<u>ዘነበች</u>** ፣ አንዱ ከአንዱ ጋር የተያያዘ ነው። ሳኒቴሽን የሚባል ነገር የሚታወቅ አይመስለኝም። በከተማዎች ውስጥ በደንብ የተዘጋጁ መጸዳጃዎች ስለሌሉ ሰው እንደፈለገው በየትም ይጸዳዳል። በተለይም ወንዝ አካባቢ. ይህ ሁኔታ ከተሰፋፋ ወደ መሬት ውስጥ በመግባት የመሬቱን ውሃ ሊያበላሽና የሰውን ጤንነት ሊያቃውስ ይችላል። ተስቦና ኮሌራ ከንጽህና ጉድለት የሚመጡ የሶስተኛው ዓለም አገር በሽታዎች ናቸው። ፈቃዱ እዚህ ላይ አጥብቆ ካልተሰራ ፣ ከውጭ አዋቂዎች አምጠተን እንዲያግዙንና እንዲያስተምሩን ካላደረግን በስተቀር ብቻችንን የምን ወጣው አይደለም። ካለበለዚያ አገሪቱ ግም በግም ትሆናለች። ተመልከት ጀርመን አገር ከሃያ ዐመት በላይ ስቀመጥ አንድ የሚከረፋ ነገር አጋጥሞኝ አያውቅም። የትም ቦታ ስሄድ ሁሉ ነገር ተዘጋጅቶ ነው የማገኘው። አገሬ ለዚህ ያለመታደሏ ግን ያበሳጨኛል። ምነው የተማረ ሰው የለም እያልኩ እራሴን እጠይቃለሁ።

**<u>ፈቃዱ</u>** ፣ ይኸውልሽ በ19ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ላይ ጀርመኖችም እንደዚህ ዐይነት ችግር ነበረባቸው። ታዲያ ውጭ በተለይ ለንደን ፣ ጣሊያንና ፓሪስ ይመላለሱ የነበሩ የጊዜው ምሁሮች በጀርመን ኋላ ቀርነት ይበሳጫሉ። በዚህ ዐይነትም ሁኔታው እንደ ማይቀጥል ይረዳሉ። ጥቂት ሰዎች ተነሳስተው ጀርመን ሙሉ በሙሉ መለወጥ እን ደለባት በማመን እንቅስቃሴ ያደርጋሉ። የታወቁ ሀኪሞችና ሳይንቲስቶች በመጀመሪያ ደረጃ የቆሻሻ መፋሰሻ የውስጥ ለውስጥ ቧንቧ መሰራት እንዳለበት በማመን ከእን ግሊዝ አገር የተማሩ ሰዎች በማምጣት ሰዎች ያሰለጥናሉ። ባጭር ጊዜም ውጤት ያሳያሉ። እንደምታይው መሰረቱ ሁሉ በዚያን ጊዜ ነው የተጣለው። እኛ ሁል ጊዜ ከማይሆን ቦታ ነው የምንጀምረው። የአንድ አገር ዕድገት የት እንደሚጀምር ፣ ምን ምን መቅደም እንዳለበት ሳንረዳ ከውጭ እያመጣን እየደረደርንና እየተከልን መጨረሻ ላይ ዛሬ የምናያትን ኢትዮጵያ ልንረከብ ቻልን። የኛ ችግር አለመጠየቅ ፣ ወደ ኋላ ዞር ብሎ አለማየት። መሰረት ሳንጥልና ሳይኖረን በሚብለጨለጩ ነገሮች ላይ መረባረብና በትንሽ ነገር ላይ መዝናናት። የኔ እህት የኛ ችግር የችግሩ መብዛትና ውስብስብ መሆን ሳይሆን እኛው ራሳችን ችግር መሆናችን ነው። ተጨባጭ ችግሮን መፍታት ይቻላል። ሰው ካመጸ ፣ የሚታይ ነገር አልታይ የሚለው ከሆነ ፣ ሊገባው የማይፈልግና የሚያላግጥ ከሆነ ምን ማድረግ ትችያለሽ ? መግደል ? ማሰር ? ወይስ ከአገር ማባረር ? ስንቱንስ አጥፍተሽ ትችያለሽ ? በጣም አሰቸጋሪ ጉዳይ ነው። ሰው ህሊናው ካልገዛው ፣ እራሱን ሊለውጥ ካልተዘጋጀ ፣ በየጊዜው ካልጠየቀ አንድን ህብረተሰብ ልትለውጭ አትችይም። የደረስኩበት መደምደሚያ የግዴታ ህዝቡን ማስተማር አለብን። ጠቅላላውን አሰራራችንን መቀየር አለብን። በስራ የሚያላግጥ መቀጣት እንዳለበት መቀበል አለብን። የአገር አደራ ተቀባዮች ፣ ገንቢዎችና ለመጪው ትውልድ አስተላላፊዎች መሆናችንን እያንዳንዱ ዜጋ እንዲረዳው ማድረግ አለብን። መፍትሄው ይህ ብቻ ነው። ስራ ፣ ስራ አሁንም ስራ !

ስራን አለመምረጥ መፈክራችን መሆን አለበት። እስቲ ተንጠልጥለው የቀሩ ለምሳሌ ስለኑሮ ውድነት ብዙ ይወራልና ብትነግሪኝ !

<u>ዘነበች</u> ፤በዕውነቱ የኑሮ ውድነት ሰማይ ላይ ወጥቷል። ሰው እንዴት እንደሚኖር በፍጹም አላውቅም። አንድ ኪሎ ስጋ ከአርባ ብር በላይ ያወጣል። አንድ ዶሮ ሰማንያ ብር ይደርሳል። ብዙ ገቢ ያለው ፣ ወይም ደግሞ እንደኛ ያለው አልፎ አልፎ ትንሽ ገንዘብ ይዞ እየሄደ እየመነዘረ እየገዛ ከሚመገበው በስተቀር ከ90 በመቶ በላይ የሚሆነው ህዝብ በጣም በዝቅተኝ ኑሮ ደረጃ እንደሚኖር መገመት ይቻላል። አንድ ኩንታል ጤፍ ከስድሰት መቶ የኢትዮጵያ ብር በላይ ያወጣል። አንድ ጠርሙስ አምቦ ውሃ አስራ ስምንት ብር ያወጣል። አንድ ብርጨቆ የፓፓዬ ወይም የብርቱካን ጭማቂ አራት ብር ያወጣል። ሆቴል ቤት ለአንድ ክትፎ ሰላሳ ብር ትከፍላለህ። ሽንኩርት ፣ ቃሪያ እፍኝ የማይሞላ ሶስትና አራት ብር ያወጣል። የሚገርመው ነገር ገበያ ስትሄድ ሁሉንም የምግብ ዐይነት ታያለህ። ዋጋው የተቆለለ ስለሆነ በፍጹም ገዝተህ ለመጠቀም አትችልም። በዚህ የዋጋ ውድነት ህዝቡ እንዴት ገዝቶ እን ደሚጠቀም በፍጹም አይገባኝም። ለዚህ የኑሮ ውድነት ከመንግሰትም ሆነ ከህዝቡ የተለያዩ ምክንያቶች ይሰጣሉ። መንግስት የሚለው ገበሬው በኑሮው እየተሻሻለ ስለመጣ እህሉን ወደ ከተማ አምጥቶ መሸጥ አይፈልግም እያለ ይለፍፋል። በሌላ ወገን ደግሞ ህዝቡ የሚለው መንግስት ከኬላ እየገዛ በተለይም የከተማውን ህዝብ ለመቅጣት የሚጠቀበት ዘዴ ነው ይባላል። የሆቴል ቤቶችን ሁኔታ ስናይ ከዚህ ከውጭ በየጊዜው የሚሄደው ሀበሻ ገንዘብ ስለሚያፈስና አንድ ትንሽ ገንዘብ ያካበተ የህብረተሰብ ክፍል ገንዘባቸውን እንደፈለጋቸው ስለሚበትኑ ነጋዴው ይህንን ለመቀራመት የሚያደርገው ከአቅርቦትና ከሱ ጠቅላላ ወጪ ጋር የማይመጣጠን ዋጋ በመጠየቁ የተነሳ ነው የሚሉም አሉ። የሆቴል ቤቶችን ቅጥ ያጣ ዋጋ መንግሰት እየተከታተለ የሚወስደው የዋጋ ቁጥጥር እርምጃ ስለሌለ የሆቴል ቤት ባለቤቶች የፈለጋቸውን ዋጋ ይጠይቃሉ። በእውነቱ ስለዚህ ጉዳይ የሰማሁትንና እኔም እራሴ ያየሁትንና የለመድኩትን ነው እንጂ ነገሩ እዚህ ደረጃ ለምን እን ደደረሰና ችግሩንስ እንዴት መፍታት እንደሚቻል መፍትሄ የሚጠቁም ሰው ባለሙያው የሆነ ተከታትሎ በጥናት መልክ ማቅረብ ያለበት ይመስለኛል። በዚህ ከቀጠለ በከተማው ውስጥ የሚታየው ድብቅ ረሀብ ከቁጥጥር ውጭ ይወጣል። የህዝቡም ጤንነት በምግብ እጦት የተነሳ እየተቃወሰ ይመጣል።

<u>ፈቃዱ</u> ፣ ከውጭ እህል ይገባል ይባላል። በተጨማሪም አዳዲስ በዘመናዊ ዘዴ የተዳቀሉ ዘሮች ይበቅላሉ ይባላል። እነዚህ ነገሮች የህዝቡን የምግብ እጥረት አያቃልሉም ብለሽ አታምኝም ?

<u>ዘነበች</u> ፣ ሙያዩ ህክምና ስለሆነ በተጨማሪም ስለምግብ ሳይንስም እከታተላሁ። እየህ እንደሚገባኝ ከሆነና አንዳንድ ባለሙያዎችም እንደሚጽፋት ከሆነ አገሪቱ ባለፋት ሰላሳ ዐመታት ከውጭ በሚመጣ እህል ጥገኛ በመሆኗ የህዝቡን የአመጋገብ ባህል ብቻ ሳይሆን ጤንነትና የሰውነት አቅዋም እየለወጠው መጥቷል። እርዳታው ችግሩን ከማቃለሉ ይልቅ በሽታን ይዞብን ነው የመጣው። ሰው እየወፈረና ተሰምተው የማይታወቁ ወይም ጥቂቱን የህብረተሰብ ክፍል ብቻ ይይዙ የነበሩ በሽታዎች እየተስፋፉ መጥተዋል። ለምሳሌ ከውጭ የሚመጣው በቆሎም ሆነ ስንዴ የስታርች መጠኑ ከፍ ያለ ስለሆነ ሰውን ያወፍራል። ለሌሎች በሽታዎችም ምክንያት ለሆን ይችላል። ሌላው የሚያሳዝነው በጂን የተዳቀለው በቆሎ በመዘራቱና በተለይም በአንዳን ድ አካባቢዎች በአዝመራው የተደነቀው እሸቱን እየጠበሰ ሲበላ ቶሎ ጡብ እያለ ነው የሞተው። ይህ ጉዳይ በጎጃም አካባቢ እንደተስፋፋና ብዙ ገበሬም ህይወቱ እንዳለፈ ይነገራል። ሌሎች በፍጹም ከኢትዮጵያ ህዝብ የአመጋገብ ባህል ጋር የማይሄዱ ምግቦች ከውጭ እየመጡ ሌላ ቀውስ እየፈጠሩ ነው። ይህ አልበቃ ብሎ አንዳንድ የአሜሪካ

ካምፓኒዎች ህዝቡን የመድህኒት መሞከሪያ አድርገውታል። የተወሰኑ ሰዎች መሞከሪያ እየሆኑ ቁመታቸው ከሚገባው በላይ ይረዝማል። ይህ ጉዳይ በጋምቤላ ውስጥ የተስፋፋና አንድ የአሜሪካ ካምፓኒ ጫካ ውስጥ በወታደር እየተጠበቀ በህዝባችን ላይ ሙከራ እያደረገ ነው። ይህንን ጉዳይ ፈቅዶ የሰጥው ያው የኛ ጉደኛ መንግስት ነው። የሚያሳዝነው ነገር ግን ይህንን ጉዳይ ወደ ውጭ ደፍሮ የሚያወጣ አንድም ኢት ዮጵያዊ ድርጅት ወይም ግለሰብ አለመኖሩ ነው። በጣም ያሳዝናል። ያቺ አገር ወዴት እንደምታመራ አይቼ። ምነው እንደዚህ ተዋረድን?
ስለጠቀላላው የምግብ ወይም እህል እጥረት ጉዳይ ስለ እርሻ ብዙም ባላውቅም አንዳንድ ቦታዎች ተዘዋውሬ ስመለከትና አንዳንድ መጽሀፎች ሳነብ አገሪቱ በማንኛ ውም ረገድ ራሷን እንደምትችል ነው የሚገባኝ። በአገራችን የማይበቅል የሰብልና የፍራፍሬ ዐይነት አይገኝም። ባለኝ ትንሽ ዕውቀት ግን የእርሻ ሚኒስትር የሚባለው የመንግስት አካል የህዝቡን የምግብ ፍላጎት ለማሟላት የሚወስደው አንድም እርምጃ እንደሌለ ነው። ተግባሩም ምን እንደሆን አይታወቅም። ሁለተኛ ዝናብ እንደ ልብ እየዘነበ ፣ ወንዝ ተትረፍርፎ እያለ ይህ ለመስኖ ለማዋል ጥረት አይደረግም። ሶሰስተኛ የገበሬው አስተራረስ ዘዴና የኑሮ ሁኔታ ለመቀየር የሚደረግ ሙከራ የለም። መንግስት የሚባለው አካል በዚህ ላይ በቂ አትኩሮ ካላደረገና የእርሻን ተግባር አስፈላጊነት ተረድቶ ወደ ገጠር አካባቢ አንድ ዐይነት የኑሮ መሻሻል እንዲታይ እርምጃ ካልተወሰደ በስተቀር ሁሉም ህዝብ በምግብ እጥረትና በአጠቃላይ የኑሮ ውድነት ይጠቃል።

<u>ፈቃዱ</u> ፣ የምትይው ሁሉ ትክክል ነው። አንደኛ በእርሻ ሙያ የሚሰለጥኑ ተማሪዎች ከገበሬው ኑሮ ጋር የሚተዋወቁ አይደሉም። ሁለተኛ ተማሪው የገበሬውን አስተራረስ ተረድቶ ገበሬው እንዴት አድርጎ ምርታማነቱን ሊያሻሽል የሚችልበትን ዘዴ እንዲማር አይደረግም። ሶሰስተኛ ፣ ተማሪዎች ቢያንስ በትምህርት ጊዜያቸው ስድስት ወር ያህል ገበሬው ዘንድ እየኖሩ አስተራረስን እየተማሩ ፣ ገበሬውም አስተራረሱን እንዲያሻሽል ምክርና ትምህርት በመስጠት ተምረው መልሰው ሊያስተምሩ የሚችሉበት ሁኔታ የለም። ተማሪው በትምህርቱ ወቅት ሰለስንዴ ፣ ስለጤፍ። ስለማሽላ አዘራርና አበቃቀል ቀርቶ ሰለ ካሮትና የቀይ ሰር አተካከል የሚማር ከሆነ ስለእርሻ ሙያ ተምሮ የሚያመጣው ነገር ምንም የለም። በተጨማሪም አሳማ በኮምፒዩተር እንዴት እን ደሚመገብ የሚማር ከሆነና ካሊፎርኒያ ወይን ስለመብቀሉ የሚነገረው ከሆነ እነዚህ ነገሮች ከአገሩ የአስተራረስ ዘዴና ባህል ጋር ምንም የሚያገናኛቸው ነገር የለም። ይህ የትምህርት መዘበራረቅና ተማሪውን ማደንቆር በዚህ ላይ ብቻ ሳይሆን በኢኮኖሚክስ ትምህርትም እንደዚህ ዐይነት ችግር አለ። ሰው የሚበላው የሚቀምሰው ነገር እየሌለ የሰው ልጅ ፍላጎት የማያቋርጥ ነው እየተባለ ትምህርት የሚሰጠው ከሆነ ፣ በቂ አቅራቢና በቂ ጠያቂ በሌለበት አገር ዋጋ በአቅርቦትና በጠያቂ መሀከል በሚፈጠር ግኑኝነት የሚደነገግ ነው ብለሽ የሚማር ከሆነ መጨረሻ ላይ ዲግሪ ስያገኝ ህዝቡን ያደነቁራል እንጂ ያለውን ዕውነተኛውን የህብረተሰብ ችግር መፍታት አይችልም። አንድ አገር እን ዴት ነው አጠቃላይ ህብረተሰብአዊ ሀብት ማፋራት የምትችለው? እንዴት ነው የምትሰለጥነው? የህዝቡስ ኑሮ እንዴት ነው ሊሻሻል የሚችለው ተብሎ መማር ሲገባ ከኢትዮጵያ ህዝብ ፍላጎት ውጭ የሆነ ትምህርት እየተማረ እንደዚህ ዐይነት ሁኔታ ውስጥ ወድቀናል። እየሽ የኔ እህት ያለው ችግር ይኽ ነው። የችግራችንን ምንጭ ምንነትና አፈታት ለመረዳት አልቻልንም። ዝም ብሎ መደነቋቆር ብቻ ሆኗል።

<u>ዘነበች</u> ፣ ፈቃዱ የምትለው ትክክል ነው። እኔም ከሙያዩ አንፃር የኢትዮጵያን ህብረተሰብ የጤንነት ችግር ስመለከተው ብዙ ነገሮች በአገር ቤት መድህኒት ሊፈወሱ የሚችሉ ናቸው። ይሁንና በዚህ ላይ ሰፋ ያለና የጠለቀ ሳይንሳዊ ጥናት አይካሄድም። መንግስትም ድጋፍ አይሰጥም። ቤለላ ወገን ደግሞ ጠቅላላው የህዝቡ ኑሮ ቀስ በቀስም መለወጥ አለበት። አንዱን ከሌላ ነጥሎ ማየት እንደማ

ይቻል አሁን ቀስ ቀስ እያለ የገባኝ ይመስለኛል። ከስረ መሰረቱ ሊለወጥና ሊሰተካከል እስካልተቻለ ድረስ የአገራችን ሁኔታ የባሰውኑ ጥምዝምዝና የሚቀጥለው ትውልድ በፍጹም ሊፈታው የማይችል ይሆናል።

__ፈቃዱ__ ፣ ስለሆቴል ቤቶችስ ንጽህና የምትሰጪው አስተያየት አለ ወይ ? እንደው ምግብ ቤት ስትሄጂ የመጸዳጃ ቦታዎችን ጎራ ብለሽ ተመልክተሻል ወይ ?

__ዘነበች__ ፣ አየህ ፈቃዱ ብዙ ጣጣ ውስጥ እያገባኸኝ ነው። ሁሉንም ዘርዝሪልኝ የምትል ከሆነ የኢትዮጵያ በሽታ ታትቶ አያልቅም። ለማንኛውም አንዳንድ ቦታዎችን ሆን ብዬ ተመልክቻለሁ። ወደ ትናንሽ ከተማዎች ስሄድ አንድ ሁለት ሆቴል ቤቶች አርፌአለሁ። የማየው ነገር ሁሉ የሚያሳፍርና የሚያሳዝን ነው። አንደኛ መጸዳጃ ቤት ስትገባ ሽታው ሌላ ነው። በፍጹም መቀመጥ አትችልም። በዚህ ዐይነት ሁኔ ታ ብዙ ሆቴል ቤቶች መዘጋት አለባቸው። ስታንደርድን የጠበቁ አይደለም። ሁለተኛ እጅህን ታጥበህ ለማድረቅ ስትፈልግ ሺህ ሰው የተጠቀመበትን ፎጣ መጠቀም አለብህ። አስበው በዚህ መልክ ሊተላለፍ የሚችለው በሽታ። ያረፍኩባቸው ሆቴል ቤቶች መጸዳዳትም ፣ መታጠብም አትችልም። በስድስት ሳምንት ቆይታ ውስጥ ሁለት ጊዜ ብቻ ነው የታጠብኩት። እንደሚገባኝ ከሆነ በየቦታወ ስሄድ ዝናብ ይዘንባል። ፈሳሽ ወንዝ አያለሁ። ይህ ሁሉ እያለ እየጠለፉ ከማስገባት ይልቅ ሰው በችግር ይሰቃያል። የሚገርመው ነገር ገንዳውም ማፍሰሻውም አለ። ችግሩ ግን ውሃውን ጠልፎ ማስገባቱ ላይ ነው። ብዙ የተማረ ሰው እያለ ይህ እንዴት ያቅተናል ? እዚህ ጀርመን አገር ከሃያ ዐመት በላይ ስኖር አንድም ቀን የውሃ እጦት አጋጥሞኝ አያውቅም። ቧንቧው ወይም አፋሳሹ የሚታደስ ከሆነ ከአስራ አምስት ቀን ወይም ከወር በፊት ቀደም ብሎ ይነገርሃል። ለተወሰኑ ሰዐታት ወይም ለአንድ ቀን በዚህ በዚህ ምክንያት የውሃ መቋረጥ አለ ይባላል። እንደምታውቀው ከጋዝ ጀምሮ እስከ መብራት ድረስ በዚህ የተቀላጠፈ መንገድ ነው የሚሰራው። ወደ ኢትዮጵያ ስትሄድ ግን ከመሻሻል ይልቅ የኋሊት ጉዞ ነው የተያዘው።

__ፈቃዱ__ ፣ እኔም የዛሬ አስራ አራት ዐመት የደረሰብኝን ጉድ ልንገርሽ። አዲስ አበባ ዘመድ አላስቸግርም ብዬ ከሆቴል ሆቴል ቤት ስሽከረከር መጨረሻ ላይ ሆቴል ዴ አፍሪቅ ከልጄ ጋር አረፍኩኝ። እቃችንን መኝታ ቤት ውስጥ አስቀምጬ እስቲ ልጸዳዳ ብዬ ወደ ባኞ ቤት ስገባ ባኞው ወይቧል። ብጫ ሆኗል። በጣም ነው የደነገጥሁት። ይህንን ዝም ብዬ መብራት አጠፋፍተን ስንተኛ ቁንጫው አላስቀምጥ አለን። ልጄ ርር ማለት ጀመረች። እኔም መተኛት አልቻልኩም። ቶሎ ብዬ ወደ ማሰተናገጃው ወርጄ ማኔጀሩን እረ ባክህን ቁንጫ እኮ አላስተኛን አለ ብዬ ስነግረው ፣ በፍጹም እንደዚህ ዐይነት ጉድ በቤታችን የለም ብሉ መለሰልኝ። ዞር ብሎ ለማንኛውም ብሎ ቁንጫዎችን ማጥፊያ የሚነፋ ነገር ይሰጠኛል። እሱን ወስጄ ስነፋ እኔም ሆነ ልጄን ማስነጠስ ጀመርን። ለትንሽ ጊዜ ያህል መተኛት አልቻልንም። እንደምንም አድረን በጠዋት ቁርሳችንን በልተን ጠፋን። ሌላው የሚገርመው ነገር ያን የመሰለ ሆቴል ምንጣፎቹ በጭራሮ ነበር የሚጠረጉት። እዚያ ላይ ጨአቱ እዚህና እዚያ ተብትኗል። ምግብ ቤት ስንገባ ምንጣፉ ከተገዛ ጀምሮ በፍጹም ተቀይሮ አያውቅም። ከአርባ ዐመት በላይ ሳይሆን አይቀረውም። ወደ ሌላ ከማምራቴ በፊት አንዳንድ ነገሮችም ብነግርሽ ክፋት ያለው አይመስለኝም። ይህ ደግሞ በባለቤቴ ላይ የደረሰ ጉድ ነው። የኔን ቤተሰቦች ለመጠየቅ ከአዲስ አበባ ወደ ጅማ በአውቶብስ ከሁለት ልጆቻችን ጋር ትሄዳለች። በዚያ አገር መንገድና አውቶብሰ ሶሰት መቶ ኪሎ ሜትር ርቀት ያለው መንገድ ወደ 10 ሰዓት ገደማ ይፈጃል። የተወሰነ ሰዓት ከተጓዙ በኋላ ወሊሶ የሚባለው ከተማ ሲወርዱ አውቶቡሰ ነጂው ተሳፋሪውን እዚህ ወርዳችሁ ምሳ መብላትና መጸዳዳት ትችላላችሁ ብሎ ይናገራል። ሁሉም ይወርዳሉ። ባለቤቴ ልጆቹን ወደ መጸዳጃ

ቤት የሚባለው ጋ ቀደም ብላ ስትገባ በጣም ከመቶሸሹ የተነሳ እየጮኸች ትወጣለች። አንዱ ያያት ኡኡ እቺ ደግሞ የማን ቀበጥ ነች ብሎ አዋርዶ አባረራት። ይህ ነው እንግዲህ የአገራችን ጉድ።

**ፈቃዱ** ፣ ሌላስ ያየሽው ፣ ያገናዘብሽውና በጭንቅላትሽ ውስጥ የሚመላለስ ነገር እንዳለ ብትነግሪኝ !

**ዘነበች** ፣ በተለይ የወጣቱ የስራ መፍታትና እየተንቀዋለሉ መዋል ነው የሚያሳስበው። መንግስት የስራ መስክ ስለማይከፍትለት ፣ ወጣቱ የቤተ ሰቡ ሸክም ሆኗል። ሲዞርና ጨአት ሲቅም ነው የሚውለው። ሌሎችም ጭንቅላት አደንዛዥ ነገሮች ተሰፋፍተዋል ይባላል። የሚወጣውና የሚገባው ስለማይታወቅ ወጣቱ የህግ-አልባና የአስተዳደር እጦት ሰለባ ሆኗ ል። ከዚህም በላይ ወጣቱ ስራ ስለሌለው የአሜሪካንን የአመጽ ቪዲዮ ሲመለከት ነው የሚውለው። ይህ ጉዳይ አስቸጋሪና ብዙ ወላጆች ሊወጡ የማይችሉት ሁኔታ መፈጠሩ ግልጽ ነው። ሌላው ለወላጆች ሸክም የሆነው ጉዳይ በተለይ ከ25 ዐመት ዕድሜ በላይ የሚሆነው ወጣት ትዳር ለመመስረት ያለመቻሉ ነው። ወንዱም እየተንቀዋለለ ስለሚውልና ምንም ገቢ ስለሌለው ቤተ-ሰብ የመመስረት ዝንባሌ በፍጹም የለውም። ፈቃዱ ሁኔታው እጅግ አሳሳቢና ህብረተሰብአችንም ወዴት እንደሚያመራ ለማወቅ አዳጋች እየሆነ መጥቷል።በአሁኑ ወቅት ወጣቱ የሚጠባበቀው ዕድል ካገኘ ወደ አሜሪካ መሄድ ነው። የዲቪ ገበያ ጦፏል። ከውጭ ገንዘብ የሚላክለት ደግሞ አዲዳስ ጫማውን እየገዛ በመሽከርከር የኤድስ ሰለባ ሆኗል። ከውጭ የሚላከው ገንዘብ ወጣቱን አባለገው እንጂ እራሱን እንዲችል አላደረገውም። በተጨማሪም የአገሪቱ ባህል በተለያዩ መልኮች እየተበላሸ ነው። በወጣቱና ጠና ባለው የህብረተ-ሰብ ክፍል መሀክል ከፍተኛ አለመግባባት አለ። በዚህ ላይ ደግሞ ትንሽ ዘመናዊ ነኝ የሚለው በ50ና በስድሳ ዕድሜ ውስጥ የሚገኝ የማይሆን ስራ ሲሰራ ይታያል። በአጭሩ ህብረተሰብአችን በጣም ተበላሽቷል። ይህንን ለማረም በፍጹም የሚቻል አይመስለኝም። የሚቻል ከሆነ ደግሞ ትልቅ ዘዴንና ውስብስብ ትግልን የሚጠይቅ ይመስለኛል። አንድ ህብረተ-ሰብ እንደዚህ ቅጥ አጥቶ ማየት በፍጹም ደስ አይልም። መንግስት ምን እንደሚሰራ ፣ የህብረተሰቡ ተጠያቂ ይሁን አይሁን ለማወቅ በጣም አስቸጋሪ ነው። ሌላው የተመለከትኩት በመኪና ከቤተሰብ ጋር ሰዞር በተለይ በአሜሪካንና በእንግሊዝ ኤምባሲ አካባቢ በቀላሉ ዝር ማለት አይቻልም። የያዙትን ግቢ ትተህ ይህን ደግሞ ስታይ የት ዓለም ውስጥ ነው ያለሁት ያሰኝሃል። አንድ ነገር ልጠይቅህና ኢትዮጵያ የሶስት ሺህ ዘመን ታሪክ አላት ይባላል። የጀግኖች አገር ነች ይባላል። ይህን ሁሉ ስመለከት በጣም ግራ ነው የሚገባኝ። ምናልባት ልታስረዳኝ ትችላለህ ወይ ?

**ፈቃዱ** ፣ አገራችን የሶስት ሺህ ዘመን ወይም ከዚያ በላይ ታሪክ ያላትና የጀግኖችም አገር እን ደነበረች አያጠራጥርም። ጥያቄው ግን ከዚህ ምን ተረፈን ነው ? ለምን እንደዚህ ዐይነት ሁኔታ ውስጥ ወደቅን የሚለውን ነው ለመመለስ መሞከር። ይህ ደግሞ ቀላል አይደለም። የብዙ መቶ ገጾችን ጽሁፍ ትንተናን ይጠይቃል። ለማንኛውም የኢትዮጵያ አብዛኛው ታሪክ የፊዩዳል ስርዓት ታሪክ ነው። ይህ ስርዓት እንደ አውሮፓው ዐይነት አዲስ የሚቀናቀነውና ዕድገትን የሚፈልግ የከበርቴ መደብ አርግዞ ሊወልድ አልቻለም። በዚህ ላይ ደግሞ ኢትዮጵያ ለብዙ ሺህ ዐመታት ከሌላው ዓለም ተገልላ በመኖሯ አዳዲስ አስተሳሰቦችን ልትቀስምና የዕድገትን ፈለግ ልትቀየስ አልቻለችም። አንዳንድ ስርዓቱን ለማደስና ለማስተካከል የተነሱ ኃይሎች ሲነሱ ወዲያውኑ ስለሚቀጩ ቦግ ማለት የጀመረው የስልጣኔ ጮራ ወዲያውኑ ይጠፋል። ይህ በእንደዚህ እያለ ሌሎች እየቀደሙን ፣ እኛ ደግሞ የነሱን ጭራ እየተከተልን እዚህ ደረስን። ከሃያኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ጀምሮ ከውጭ ወደ ውስጥ የገባው የባህል ተጽዕኖ በመሰረቱ ኢትዮጵያን ሊያራምዳትና የስልጣኔ ባለቤት ሊያደርጋት የሚችል ኃይል ብቅ ብሎ እን ዲወጣ የሚያደርግ አልነበረም። እዚያው በዚያው የድሮው ሁኔታ እንዲዳሽቅ ፣ በሌላ ወገን ደግሞ ስልጣኔ ምን እንደሆነና አንድ ህብረተሰብስ እንዴት እንደሚገነባ ሊገነዘብ

የማይችል እጅግ አደገኛ ኃይል ብቅ አለ። ይህ የንጉሱ-ነገስቱን አገዛዝ ተገን በማድረግ ፣ በአንድ በኩል በህዝብ ላይ የሚቀልድ ፣ በሌላ ወገን ደግሞ አገሪቱን እየሰረሰረ ለውጭ ኃይል የሚሸጥ ሆነ። በዚህ በተተራመሰ ሁኔታ ውስጥ ነው የተማሪው እንቅስቃሴ የተጸነሰውና አዲስ መፈክር ይዞ በመውጣት አገዛዙን መጋፈጥ የጀመረው። በአጭሩ የአፄው አገዛዝ ስልጣኑን አላመጣም። የነበረውን ዕድል አልተጠቀመበትም።

__ዘነበች__ ፣ አየኽ ፈቃዱ እዚህ ላይ ነው ከአንተ ጋር የማልስማማው። እንደሚባለውና ከቤተሰቦቼ እንደሰማሁት ከሆነ አፄ ኃይለስላሴ ናቸው ኢትዮጵያን ከውጭው ዓለም ጋር ያስታወወቁና ስልጣኔም በብዛት እንዲገባ አመቺ ሁኔታ የፈጠሩት። የተማሪው እን ቅስቃሴ ኢዝም የሚባል ነገር ፈጥሮ- ፊዩዳሊዝም ፣ ካፒታሊዝም ፣ ኢምፔሪያሊዝም- ኢትዮጵያን መቀመቅ ውስጥ ነው የከተተው። ለምሳሌ ፊዩዳሊዝም የሚባለው ጽንሰ-ሃሳብ እናንተ የፈጠራችሁትና በአባቶቻችን ላይ እንድተንሱ የተጠቀማችሁበት የትግል መሳሪያችሁ ነው። ይህ ዘመቻችሁና በአገዛዙ ላይ በጭፍን በመነሳታችሁ ነው አገራችን የዛሬውን ጽዋ ልትቀመስ የተዳረገችው። በአጭሩ የእኔ አስተያየት ይህ ነው።

__*ፈቃዱ*__ ፣ የኔ እመቤት በሰፊው ስናወራ የተግባባን መስሎኝ ነበር። ይቅርታ አድርጊልኝና ታጥቦ ጭቃ የሚባለው ሁኔታ ውስጥ እየገባን ነው። ነገሩ በቀላሉ የሚፈታና ልትረጂው የምትችይው ነገር አይደለም። በመጀመሪያ ግን አሁንም ላረጋግጥልሽ የምወደው እን ደምታይኝም የተማሪው እንቅስቃሴ ጀማሪ አይደለሁም። የኋላ ኋላ ሲጨልም የገባሁና ትግሉን የተቀላቀልኩኝ ነኝ። ሆኖም በአጭር ገዜ ውስጥ ብዙ ነገር ለመማር ችያለሁ። ጠቃሚውንም ጎጂውን ም ለመመልከትና ትምህርት ለመቅሰም ችያለሁ። በተረፈ ግን እን ዲያው የወሬ ወሬ የተማሪውን እንቅስቃሴ በደፈናው መወንጀል አይቻልም። መጠየቅ ያለብሽ የተማሪው እንቅስቃሴ ይህንን አይነቱን የትግል ፈለግ እንዲከተል ምን ገፋፋው ? ሌላስ አማራጭ መንገድ አለነበረም ወይ ? ያነሳቸውንስ የትግል መፈክሮች በዝርዝርና ጠለቅ ብሎ አጥንቷል ወይ ? እነዚህ ነገሮች ላይ ነው መወያየት ያለብን። አየሽ ምክን ያቱን እስካላወቅን ድረስ የምንሰነዝረው ውንጀላ ለችግራችን መፍትሄ ሊሆን አይችልም። በአጠቃላይ ሲታይ የተማሪው እንቅስቃሴ ያነሳቸው ለምሳሌ እንደ መሬት ላራሹ ጉዳይች አስፈላጊና ታሪካዊም ነበሩ። ጥቂት የመሬት ከበርቴዎች ብዙ መሬት ይዘው አብዛኛው ህዝብ በድህነት ይማቅቅ እንደነበር አሌ አይባልም። ችግሩ ግን ብዝበዛ የሚለው ጽንሰ-ሃሳብ ሲተነተን ብዙ ያልታዩ ነገሮች ነበሩ። በተጨማሪም በመፈክር ደረጃ ለምሳሌ ይውደሙ የሚለው አነጋገር የሚያስፈራራ ነበር። ፊዩዳል የሚባለውን መደብ ስተውስዲ ደግሞ አንድ ወጥ አልነበረም። ከቦታ ቦታ የሚለያይ ብቻ ሳይሆን በኑሮው ደረጃም እጅግ የሚለያይ ነበር። አብዛኛው የፊዩዳል መደብ ጥሩ ምግብ ከመመገብ በስተቀር በሌሎች ነገሮች ከገበሬው የሚለይ አልነበረም። መሬትና እህል የሚያካብት እንጂ የገንዘብ ሀብት አልነበረውም። ጭቆናውም ቢሆን ተጋኖ ነበር የሚወራው። በፊዩዳሉና በገበሬው መሀከል የነበረው ግኑኝነት የላላ ነበር። ከዚህ በላይ የተወሰነው የፊዩዳል መደብ ከህብረተሰቡ ጋር የነበረው ግኑኝነት የጠበቀ ነበር። ሰርግ በመደገስ ፣ አንዳንድ በዓላትን አሳቦ ድግስ በመደገስ ከሌለው ህብረተሰብ ጋር የነበረውን ግኑኝነት በዚህ መልክ ያካክስ ነበር። እዚህ ላይ ነው የተማሪው እንቅስቃሴ በጅምላ ተነስቶ የስርዓቱን ምንነት ጥለቅ ብሎ ሳይመረምር ወደ አንዳች ድምደማ ላይ የደረሰው። ከዚህ በተረፈ በተማሪው እን ቅስቃሴ መሀከል ፣ ልክ ዛሬ እንደምናየው መደማመጥ ባለመኖሩና ስር የሰደደ ሳይንሳዊ ጥናት እንዳይካሄድ መንገዱ ሁሉ ስለተዘጋ በሩ ለአመጽ ተከፈተ። ጥቂት ኃይሎች ሁኔ ታውን ለማርጋት ሙከራ ቢያደርጉም ሁኔታው ከቁጥጥር ውጭ በመውጣቱ እንደዚያ ዐይነት አስከፊ ሁኔታ ሊፈጠር ችሏል። እዚህ ላይ ግን ይኸኛው ነው አጥፊ ብሎ አንዱ ላይ ብቻ ጣት መሰንዝር አይቻልም። ችግሩ የታሪክን ኃላፊነት በሚገባ ካለማጤን የተከሰተ የማያስፈልግ ሽኩቻ ነው። የህዝባችንን ስነ-ልቦና በቅጡ መረዳት አልተቻለም። የውጭው ኃይል በአገራችን ላይ ሊያስከትል የሚችለውን አደጋ በፍጹም ግንዛቤ ውስጥ አልገባም። ከሰላሳ ዐመት በኋላም ይህ ችግር አፍጦ አግጦ ይታያል።

የዛሬው ትውልድ ደግሞ የዓለም ፖለቲካና በስተጀርባው የሚውጠነጠነው ነገር በፍጹም አልገባውም። ካላንዳች መመሪያ ዝም ብሎ የሚጋልብ ነው።

የኔ እመቤት ነገሩን በጣም አሳጠርኩት ። ደግሞም ብዙ መሻሻል ቢታይብሽም አንድ ጊዜ በጭንቅላትሽ ውስጥ የቀረጽሽው ነገር ስላለ እኔ የምለፈልፈው ሁል እንደቅዠት መስሎ ነው የሚታይሽ። ይህ ደግሞ አይገርምም። በብዙ ሰዎች ዘንድ የሚታይና ትላንትና በአንድ መፍክር ስር ያልታገሉትን ያህል መቶ ሰማንያ ዲግሪ ዞረው በታገሉለት መፈክር ላይ ዘመቻ ሲያካሄዱ ይታያሉ። እንደዚህ ስልሽ አይሻሻሉ ማለቴ አይደለም። ቀኝ አቋም ከመውሰድ ነገሮችን አንድና ሁለት ጊዜ ቢያሰላስሏቸው ይሻላል ለማለት ያህል ነው።

<u>ፈቃዱ</u> ፣ ወደ ሌላ ጥያቄ ላምራ። ሌላስ ፎቅ ቤቶች በብዛት ይሰራሉ። መንገዶችም እንደዚሁ። እዚህ ላይ የምትሰጪው አስተያየት አለ ?

<u>ዘነበች</u> ፣ በዕወነቱ ቤትም ሆነ መንገድ ሲሰራ የሚቃወም የለም። ይህ ለአንድ አገር ዕድገት አስፈላጊ እንደመሆኑ መጠን መሰራት እንዳለበት የሚያጠያይቅ አይደለም። ጥያቄው እዚህ ላይ እዚህና እዚያ የሚሰሩት ፎቅ ቤቶች በደንብ የተጠኑ ናቸው ወይ ? ትላልቅ ፎቆችስ መሰራታቸው አስፈላጊ ናቸው ወይ ? ጥራትና ውበት አላቸው ወይ ? ለአደጋስ የተጋለጡ ናቸው ወይስ አይደሉም ? ከፎቅ ቤቶች በስተጀርባ ያሉትስ ቆሻሻ ቤቶች ጉዳይ ? በዚህ ላይ ብዙ ዕውቀት ባይኖረኝም ጀርመን አገርና አንዳንድ የአውሮፓ አገሮች ካሉት የህንፃ አሰራር ጋር ሳወዳድራቸው ውበታቸውና ጥራታቸው እዚህ ግባ አይባልም። ለምሳሌ የመሬት መንቀጥቀጥ ቢመጣ ብዙ አደጋ ሊደርስ ይችላል። በተጨማሪ አብዛኛዎቹ ፎቅ ቤቶች አገር ውስጥ በሚመረቱ ማቴሪያሎች አይደለም የሚገነቡት። አገር ቤት ውስጥ ሁሉ ነገር እያለና ማምረት ሲቻል ሁሉም ከውጭ ማቴሪያል ይጠብቃል። ስለዚህም ብዙ ቤቶች ተጀምረው ቆመው የቀሩ አሉ። የመንገድ አሰራሮችም ብዙ ጥራት የሚጎላቸው ብቻ ሳይሆኑ ለሰው ታስበው የተሰሩም አይመስሉም። በዚህም ምክንያም ብዙ ሰው በመኪና አደጋ ይሞታል። እኔ ባለኝ ትንሽ ዕውቀት ይህንን ነው መመዝገብ የቻልኩት።

<u>ፈቃዱ</u> ፣ ይህ ጉዳይ በብዙ እዚህ አውሮፓ ውስጥ በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የሚነሳ ጥያቄ ነው። ግንዛቤሽም ትክክል ይመስለኛል። በተለይ የሚገርመኝ ነገር አንድ ሰሞን ሲሚንቶ ጠፋ ተብሎ ስራ ሁሉ ቆሞ ነበር። የሚያሳዝነውና የሚገርመው ነገር እን ዴት ሌላ ዘዴ አይፈለግም። እየሽ እዚህ አውሮፓ ውስጥ ከስድስት መቶ ዐመት ወይም ከዚያ በፊት የተሰሩ ትላልቅ ካቴድራሎችንና ቤተ-መንግስቶችን ለተመለከተ በዚያን ጊዜ ስሚንቶ ስለነበር አይደለም ይሰሩ የነበረው። ጊፕስ የሚባል ከመሬት ውስጥ ተቆፍሮ የሚወጣ ማጣበቀያና ከወንዝ አካባቢ የተኛ ደለል እሱን በመሰብሰብና በማጓዝና አብሮ በማቡኳት ነበር ቤቶች ሲሰሩ የነበረው። ሲሚንቶ የመቶ ዐመት ዕድሜ አይሞላውም። እኛ አገር ከላይ የጠቀስኳቸው ማቴሪያሎች በየቦታው አሉ። ይህ ብቻ ሳይሆን ለጡብ የሚሆንም አፈር ተትረፍርፎ ይገኛል። ዕብነ-በረድና ለህንፃ ስራ የሚያገለግል ልዩ ልዩ ዐይነት ዲንጋይ እያለ እነዚህን ሁብቶች በሙሉ በስነስርዓት የመጠቀም ባህል የለንም። ሁሉም ነገር ከውጭ አልቆ መምጣት አለበት። በዚህ መልክ ባላፉት አስራ ስድስት ዐመታት ብብዙ ቢለዮን ዶላር አገሪቱ ከስራለች ማለት ይቻላል። ይህ የኛ ችግር ብቻ ሳይሆን የብዙ አፍሪቃ አገሮችም ችግር ነው። ጥሬ ሀብትን ማኔጅ የምንችል አይደለንም። ዘይት አገር ውስጥ እያመረቱ ቤንዚን ከውጭ የሚያመጡ አን ዳንድ የአፍሪቃ አገሮች አሉ። በዚህ መልክ አንድን አገር በተስተካከለ ሁኔታ በፍጹም ማሳደግ አይቻልም። ይህ ነው ባጭሩ እኔም የተገነዘብኩት።

**ዘነበች** ፤ታዲያ ችግሩ እንደዚህ ውስብሰብና ግልጽ ከሆነ ለዛሬው ችግር መፍትሄ ይሆናል ብለህ የምታስበው ነገር ምንደነው? የትኛውስ ኃይል አሁን ካለችበት ጭን ቀት አገራችንን ሊያወጣት ይችላል ብለህ ታምናለህ? የውጭ ኃይሎችስ የአገራችንን የወደፊት ዕድል በሚመለከት የሚጫወቱት ሚና ምን ይመስልሃል ? ትግሉንስ ሊያግዙ ይችላሉ ወይ? ለዕድገታችንስ ዕንቅፋት ወይም አጋዥ ሊሆኑ ይችላሉ ወይ ? እነዚህን ጥያቄዎች ብትመልስልኝ ደስ ይለኛል።

**ፈቃዱ** ፤ዘነበች ያነሳሻቸው ጥያቄዎች ከባድ ብቻ ሳይሆኑ ብዙ የጭንቅላት ስራን የሚጠይቁ ናቸው። እንደዚህ በቀላሉ የሚመለሱ አይደለም። ቀደም ብዬ እንዳልኩሽ የችግሮቹ ውስብስብነትና መደራረብ አይደለም ችግር የሚፈጥረው።በኛ ጭንቅላት ውስጥ የተጋገረውና የተጣመመው አስተሳሰብ ነው የችግራችንን ምንጭ እንዳንረዳ ቆልፎ የያዘን። የግሪክ ፈላስፎች እንደሚሉት ጭንቅላት ካላየ ዐይን ማየት አይችልም። በሌላ አነጋገር የአንድን ቸግር ምንጭ ልንረዳ የምንችለው በትክክለኛ ፍልስፍና ስንመራ ብቻ ነው። ትክክለኛ ፍልስፍና እስካልጨበጥን ድረስ የተሳሳተ ትንተና ብቻ ሳይሆን ወደ ተሳሳተ መፍትሄ እናመራለን። ሁሉንም አጠቃሎ መወንጀል ባይቻልም ዛሬ እንደማየው ከሆነ ነገሮችን በቅጡ የማጤን ፣ የመወያየትና የመደማመጥ ባህል የለም። በዚህ ላይ ደግሞ ትግላችን በሃሳብ ዙሪያ የሚሽከረከር አይደለም። ሳይንሳዊና የቴዎሪ መሰረት እጅግ ያንሰዋል። እንደዚህ ዐይነቱ ቲዎሪና ሳይንሰ-አልባ ትግል ለረጅም ጊዜ እንደሚቀጥል ጥርጥር የለኝም። አብዛኛው ቦታ ኋላ-ቀር አስተሳሰቦች እያገረሹና ትግሉ ፈሩን እየለቀቀ ነው። በሌላ ወገን ደግሞ ችግር አለ ተብሎ ተፍርቶ አይታለፍም። ወይም ዝም ብሎ እጅን አጣጥፎ መቀመጥ አይቻልም። በተለይ አንቺም ሆነ ሌሎች ማወቅ ያለባቸው ነገር ፖለቲካ ከፍተኛ ጥበብን(Wisdom)የሚጠይቅ ቢሆንም ከይሉኝታ ውጭ መሆን አለበት። ማንኛውም ግለሰብ በፖለቲካ ዓለም ውስጥ ገብቼ እሳተፋለሁ የሚል ሁሉ ከመጀመሪያውኑ መቀበል ያለበት ነገር የፖለቲካ ትግል በጭፍንና በጥላቻ ላይ ሳይሆን በዕምነት ላይ የተመረኮዘ መሆን አለበት።

አንቺም ፣ ሌሎችም እኔም የፖለቲካ ሰዎች ሆን አልሆን የተወሰኑ አስተሳሰቦችንና እሴቶችን እንከተላለን። እንቀበላለን። አንዳንዶቻችን የፖለቲካ ውጥንቅጥ ውስጥ ሳንገባ እንኖራለን። ከዚህም ከዚያም ለመሆን አንፈልግም። ሌሎች ደግሞ እንደሁኔ ታው ባህሪያቸውን የሚለዋውጡ ፣ ከዚህም ወይም ከዚያኛው ጋር ለመሆን የሚሹ አሉ። ከዚህ ወጣ ስንል ደግሞ ኃላፊነትን ለመሸክም የሀቀኛውን መስመር ይዘን እንታገላለን የሚሉ አሉ። የአብዛኛው ሰው አስተሳሰብ በዚህ ክልል ውስጥ ቢሆንም በፖለቲካ ቲዎሪ ውስጥ ሁለት መስመሮች እንዳሉ ግልጽ ነው። ሁለቱም መስመሮች ሀቀኛ ነን ቢሉም ከህዝብ ጥቅም አንፃር የፖለቲካ ትግልን አቅጣጫ ለመቀየስ በሚጥሩና የግለሰብኝነትን ሚና ብቻ አጉልተው በማሳየት በህዝብና በግለሰቦች መሀከል የሚኖረውን መተሳሰር በማዛነፍ የዲሞክራሲን ትርጉም ውስጣዊ ይዘት አጣመው ህዝብን የሚያሳስቱ እንዳሉ በዓለም ላይ የተደረጉትና የሚደረጉት ትግሎችና የምናያቸው ተጨባጭ ሁኔታዎች ጉልህ ምስክሮች ናቸው። እዚህ ላይ ነው ብዙ ሰዎች የሚሳሳቱትና ገደል የሚገቡትም። ለዚህም ነው ዛሬ በየቦታው የሚካሄዱትን ጦርነቶች መነሾ ለመረዳት ለብዞዎቹ አስቸጋሪ እየሆነ የመጣው። ከዚህ ስንነሳ ፖለቲካ በዛሬው ሁኔታ አንድን ህዝብ ነፃ የሚያወጣ መሳሪና ማንነቱን የሚያረጋግጥበት መሆኑ ቀርቶ ወደ ንግድነት ነው የተለወጠው።

ከዚህ ስንነሳ በመጀመሪያ በእኔ ዕምነት መደረግ ያለበት በሃሳብ ዙሪያ የሚደረግ ውይይት እንደመሰረተ ሃሳብ በብዞዎቻችን ጭንቅላት ውስጥ መያዝ አለበት። በሃሳብ ዙሪያ የማይደረግ ውይይት የኋላ ኋላ ወደ ሽፍጠኝነትና አገር ወደ ማፈራረስ ያመራል። በሃሳብ ዙሪያ የሚደረግ ውይይትና ክርክር ጥራትን መስጠት መቻሉ ብቻ ሳይሆን የህብረተሰብአችንን አቅጣቻና አገነባብ መልክ ለማሲያዝ ያመቻል። በዚህ ላይ ደግሞ እያንዳንዱ ድርጅትም ሆነ በፖለቲካ ዓለም ውስጥ ገብቶ እታገላለሁ የሚል ግለሰብ

ለየትኛው ህብረተሰብ እንደሚታገልና ዕምነቱስ ምን እንደሆነ በግልጽ ማስቀመጥ አለበት። የፖለቲካ ፕሮግራምና ጊዜያዊ መግለጫዎች በራሳቸው ለአንድ ህብረተሰብ ምስረታ የጥራት መሰረት ሊሰጡት በፍጹም አይችሉም። ኢትዮጵያ አገሬ እያሉ ባንዲራ ማውለብለብ ብቻ በቂ የትግል መስመር ሊሆን አይችልም። እዚህ ላይ ሰዎችን ለማባረርና ለማካረር ሳይሆን አገራችን በሳይንስና በቴክኖሎጂ እንድታብብ ከተፈለገ ፣ ጠንካራና የምትከበር እንዲሁም ሰላም የሰፈነባትን ኢትዮጵያ የምንሻ ከሆነ የላይኛው የትግል ዘዴ ሊታለፍ የማይችል መሰረታዊ ጉዳይ መሆኑን ለማመልከት ነው።

ይህ ግልጽ ከሆነ ፣ መንግስት ማለት ምን ማለት ነው ? ተግባሩስ ምንድነው ? አገርና ህብረተሰብ ማለት ምን ማለት ናቸው? ለብሄራዊ ነፃነት የሚደረገው ትግልስ ምን መምሰል አለበት ? ብሄራዊ ነፃነትስ ስንል ምን ማለታችን ነው? አንድ ህብረ-ብሄር እንዴት ይገነባል? የህብረ-ብሄር ዋናው መሰረቱ ምን ምን ነገሮች ናቸው ? አንድ ብሄራዊ ኢኮኖሚ እንዴት ይገነባል ? ብሄራዊ ሀብት እንዴት ማካበትና ማሳደግ ይቻላል ? አዳዲስና ዘመናዊ ከተማዎች እንዴት መገንባት ይቻላል? ወይስ ኢትዮጵያ አሁን ባለው የተዝረከረከ የከተማና የመንደር አመሰራረት መቀጠል አለባት ወይ ? በግለሰብና በህበረተሰብ መሀከል ስላለው ግኑኝነት ምን መፍትሄ ልንሰጥ እንችላለን? ቴኪኖሎጂዎችን ስለመፍጠርና ከውጭ ስለማስገባት ጉዳይ? ህዝቡን በስራ የማሳተፍ ጉዳይ ? በዚህ ላይ መንግስት ስለሚኖረው ሚና… ወዘተ. እያለን ብዙ ጥያቄዎችና ሃሳቦች መሰንዘርና መወያየት አለብን። ይህ ሳይሆን ዝም ብሎ ወደፊት መሄድ በፍጹም አይቻልም።

ይህ ግልጽ ከሆነ በዚህ ዐይነት መልክ መደራጀትና መታገል ያስፈልጋል። ውድ እህቴ የን ጹህ ሰዎች አስተሳሰብ በመጀመሪያ ለስልጣን መታገል መሆን የለበትም።ወይም ቀደም ቀደም ብሎ መታየት አይደለም። የአዋቂዎች የትግል ዘዴ ለስልጣኔ የሚያመቸውን መን ግድና ለዚህ ደግሞ አዳዲስና የተሻሉ ሃሳቦች መሰንዘር ነው። በዚህም ላይ ስምምነት ካለ ኢትዮጵያን ማን ይግዛት የሚለው አይደለም የሚያሳስበው። አሁን ባለው ሁኔታ ደርጅቶች እንደ አማራጭ ሆነው ሊቀርቡ ይችላሉ ወይ ነው ? ይህንን ሳነሳ መጀመሪያ ከዝቅተኛ ሁኔታ መነሳት እንዳለብኝ በማመን ነው። ሌሎች ነገሮች ሁሉ ፣ መደማመጥ እሳካለ ድረስ በልምድና በትምህርት የሚደረሱ ናቸው። በተጨማሪም የአንድ አገር ግንባታ በአንድ ትውልድ የሚጠናቀቅ አይደለም። እንደምታይው ዓለም ውሰብስብና አስቸጋሪ እየሆነች ነው የመጣችው። እዚህ ላይ ደግሞ አዳዲስ ኃይሎች ብቅ እያሉና አዳዲስ ነገሮችን እየነዙ ዓለምን እያዋከቡ ነው። ስለዚህ ህብረተሰብን የመገንባቱ ጉዳይ አሰቸጋሪና ውጣ ውረድ የበዛበት ይሆናል ማለት ነው። ከዚህ ስነሳ ያለውና የዛሬውን አገዛዝ የሚቃወመው የተወሰነው ኃይል እንደ አማራጭ ሆኖ ሊቀርብ ይችላል። በብዙ ረገድም ከዛሬው አገዛዝ የተሻለ ዕውቀትና ርዕይ አለው። ዋናው ነገር ግን ጥራት ባለው መልክ ይህንን የተበታተነ ኃይል እንዴት መሰብሰብ ይቻላል የሚለው ነው። እዚህ ላይ ነው እን ግዲህ ብዙ ስራ መሰራት ያለበት።

የውጭ ኃይሎችን ሚና በሚመለከት በኩል ብዙም ጥናት የተካሄደ አይመስለኝም። አንዳንድ የዓለም የፖለቲካ ኃይል አሰላለፍ የሚያውቁና በደንብ የገባቸው ግለሰቦች እንዳሉ ባያጠራጥርም አብዛኛው ኢትዮጵያዊ የዓለም ሁኔታ የተዘበራረቀበት ይመስላል። ዓለም የመወዳደሪያ መድረክ መሆኑን ሊገነዘብ በፍጹም አይፈልግም። ዓለምን አንድ ወጥ አድርጎ የሚመለከትና ካለግሎባላዜሽን የሚያዋጣ ነገር የለም ብሎ ሽንጡን ገትሮ የሚታገል አል። ሌላው ደግሞ ኢትዮጵያን የአሜሪካ ተቀጥያ ለማድረግ የውስጥ ደባ የሚያደርግ አለ። ኢትዮጵየያ ካለ አሜሪካ ነፃ ለመውጣት እንደማትችል አምኖ የተቀበለ አለ። አሜሪካ ጦርነት ፈልፋይ ፣ ህብረተሰብ አዘበራራቂ መሆኑን የማይገነዘብ ሺህ በሺህ የሚቆጠር ኢትዮጵያዊ እዚህና እዚያ አለ። አሜሪካን ሆኖ አሜሪካን ውስጥ ያለው ሁኔታ ምን እንደሚመስል ለመገንዘብ የማይፈልግ አለ። ይህ ኃይል የፖለቲካውን መድረክ እየያዘው በመምጣት ላይ ነው። ያም ሆነ ይህ እያንዳንዱ አገር በራሱ ህይወት ላይ መወሰን መቻል አለበት። የተፈጥሮ ህግም የሚያዘው ይህንን

ነው። አንድ ሌላ ኃይል ከውጭ መጥቶ ኢትዮጵያን ነፃ ሊያወጣና ለህዝብ የተደላደለ ኑሮ ለሚሰርትላት አይችልም። ምንአልባት ተገንዝበሽ እንደሆን ዓለም በጥቂት ኃይሎች የምትሽከረከር ነች። እነዚህ ኃይሎች የተለያዩ ዓለምአቀፋዊ ኢንስቲቱሽኖችን እዚህና እዚያ አቋቁመው የዓለምን ህዝብ ፍዳ እያሳዩት ነው። ቢያንስ ባለፉት ስድሳ ዓመታት የምንመለከተው ሀቅ ይህ ነው። ይህንን የሚክድ ካለ ወይ ዐይኑ የታወረ ፣ ወይ የማይገባው ፣ ካሊያም ደግሞ እልም ያለ አድር ባይ መሆን አለበት።

ከላይኛው አጭር ዘገባዬ ስነሳ ማንም የወጭ ኃይል የኢትዮጵያን ዕድገትና እን ደህብረተሰብ ተጠናክሮ መኖርና መራመድ በፍጹም አይፈልግም። በዚህም በዚያም አታሉ የድህነቱን ዘመን ካማራዘም በስተቀር። በሌላ ወገን ግን የፖለቲካ ሰው እን ደመሆኔ መጠን ነገሩን እያጠኑ በግልጽ ወደ ውስጥ እየተወያዩ ጥቅም ማግኘት ይቻላል ይጠቅሙናል ብለን ከምናምናቸው አገሮች ጋር ጥሩ ግኑኝነት መመስረት ይቻላል። የዛሬው የጦፈው የዓለም አቀፍ የጥሬ ሀብት ውድድር ፣ እንደ ቻይና ፣ ህንድ ፣ የራሺያ እንደገና ማንሰራራት ፣ ብራዚልና ሌሎች አገሮች እየተጠናከሩ መውጣት ለእንደኛው አገር አመቺ ሁኔታን ፍጥሯል። ይህም በመሆኑ የእነ ዓለም ባንክና የፈንዱ እንዲሁም የዓለም ንግድ ድርጅት ሚና ጥያቄ ውስጥ እየገባ መጥቷል። የዛሬዋ ዓለም የትላን ትናዋ ዐይነት አይደለችም። ስለዚህም እንደሞኝ ፍቅር ከአሜሪካ ጋር የሚያላግገን ጉዳይ በፍጹም ሊኖር አይችልም። ሰላምን ወደ ሚሹ ፣ ብዙ ውስብስብ ጥያቄዎችንና የአሰራር ስልቶችን እያንጋጉ ወደ ማያመጡ አገሮች ጋር ፊታችንን ዞር ማድረግ አለብን። እዚህ ላይ ለአገራችን የወደፊት ዕድገት ከጎረቤት አገሮች ጋር የሚኖረን ግኑኝነት ወሳኝ ሚናን ይጫወታል። በተቻለ መጠን መልካም ጉርብትናንና ጦርንትን ወደ ማያመጣ ፖለቲካ ማምራትና መንገዱን መቀየስ አለብን። በአካባቢያችን የሚካሄዱት ጦርነቶች የውክልናና ካለመግባባት የሚፈጠሩ የወንድማማች ጦርነቶች ናቸው። ወድ እህቴ እኛ የአሜሪካንን ጦርነት በሬሞት ኮንትሮል እየተቆጣጠረን ማካሄድ የለብንም። ጦርነቱ የሚካሄደው እኛ ምድር እስከሆነ ድረስ አሜሪካ ጉዳዩ አይደለም። እኛ ኢትዮጵያኖች ከዚህ የአሜሪካን እቡይ ተግባር መላቀቅ አለብን። በዚህ ከቀጠለ የፓኪስታን ሁኔታ ውስጥ እንገባለን። ባጭሩ የመሰጥሽ መልስ ይህ ነው።

**<u>ዘነበች</u>** ፣ ፈቃዱ በሰጠኸኝ መልስ ረክቻለሁ። አላሰልችህና መጨረሻ ላይ ሁለት መሰረታዊ ጥያቄዎች ልጠይቅህ። በተለይ ከአገር ቤት ከተመለስኩ በኋላ እረፍት አልሰጥም ያሉኝን ነገሮች ፤ ድህነቱን ፣ ቆሻሻ ቦታዎችን ፣ የህዝቡን የተመሰቃቀለ ኑሮ ፣ በሀዘን ፊቱ መጨማደድ. የወጣቱን ተስፋ መቁረጥ ስመለከት የኑሮ ትርጉም ምንድ ነው ብዬ እንደ ጠይቅ ተገድጃለሁ። ለመሆኑ የኑሮ ትርጉሙ በዚህ ዓለም ላይ ምንድን ነው?

**<u>ፈቃዱ</u>** ፣እየሽ የኔ እህቴ ቀስ በቀስ ወደ ፍልስፍና ውስጥ እየከተትሽኝ ነው። በጣም ጥሩ ጥያቄ ነው። አዎ አብዛኛዎቻችን በዚህች ዓለም ላይ ስንኖር ለምን እንደምንኖር አን ጠይቅም። እንዲያው ለመኖር የምንኖር ነው የሚመስለን። የህይወትን ትርጉም ለመረዳት እያንዳንዱ ሰው ሶስት መሰረታዊ ጥያቄዎችን ማንሳት ያለበት ይመስለኛል። ይኸውም ከየት እንደመጣ ፣ ለምን በዚህች ዓለም ላይ እንደሚኖርና ወዴትስ እን ደሚያመራ ! እስከሚገባኝ ድረስ እያንዳንዳችን በዚህች ዓለም ላይ ብቅ ስንል ትርጉም አለን። የሰው ልጅ አካል እንደመሆናችንም መጠን ለመፈጠራችን ምክንያት አለው። ዝም ተብሎ የተወረወርን አይደለንም። አብዛኛዎቻችን ግን ይህንን አንረዳም። ጥያቄም አንጠይቅም። አንዳንዶቻችን ሰው እየገደልን ፣ እያሰቃየንና በዚህ እየተደሰትን የምንኖርና ይህም ትክክለኛው የኑሮ ትርጉም የሚመስለን አለን። እንዲሁም ጥቂቶቻችን ደግሞ የሰው ልጅ ለጦርነት የተፈጠረና ጦርነትም የተፈጥሮ ህግ የሚመስለን አለ።ሌሎቻችን ደግሞ የአብዛኛውን ህዝብ ሀብት እየዘረፍን ፣ እኛ በደስታ እየኖርን ፣ የሌላውን ስቃይ እያየን የምንኖር አለን። ይህም ትክክለኛው የኑሮ ዘዴ የሚመስለን አለ።

*ብዞዎቻችን ደግሞ ከቀን ወደቀን ፣ ከሳምንት ወደ ሳምንትና ከወራት ወደ ወራት ምንም ሳንሰራ እጃችንን አጣጥፈን ኑሮን በመጽዋት የምንገፋ አለ። ለዚህ ሁሉ የኑሮ ትርጉም ማጣት ፣ አብዛኛው ህዝብ ካለምንም ስራ እየተንቀዋለለ እንዲኖር ማድረግ ተጠያቂዎችም በየአገሩ የሰፈኑ የተደናቆሩ አገዛዞች ናቸው። ለምን ስልጣን ላይ እንደወጡ የማይረዱና አንድን ህዝብ እንዴት ማስተዳደር ይቻላል ብለው የማይጠይቁ። ይሁንናም ይህ ሁሉ እያለ የኑሮ ትርጉምንም የሚጠይቁና የሰው ልጅ ከእንስሳ የሚለይበትን የሚያስተምሩና መስመር ለማሲያዝ የሚጥሩ እንዳለ የታወቀ ነው። እነዚህ ቁጥራቸው አነስተኛ ቢሆንም ፣ የሰው ልጅ በአፈጣጠሩ ስነ-ምግባራዊ እንደሆነና*(ethical being) *ጥበባዊ እንደሆነ ያስተምራሉ። ስነ-ምግባራዊ የሚያሰኘው የምርት መሳሪያዎችን ስለሚሰራና አካባቢውንም ለመለወጥ ስለሚችል ነው። ጥበባዊ የሚያሰኘው ነገር ደግሞ ቆንጆ ቆንጆ ነገሮችን ለመስራት የሚችል ፍጡር በመሆኑ ነው። በዚህች ዓለም ላይ መጥፎ ነገርን የሚመኝ የለም። ሁሉም ሰው በደስታ መኖርን ይፈልጋል። የተሻለን ኑሮ ይመኛል። እነዚህን ነገሮች ግን ተግባራዊ እንዳናደርጋቸው የሚከለክሉን ነገሮች አሉ። አስተሳሰባችን ርቆ ሊሄድ አይችልም ይሆናል። በተወሰኑ ነገሮች እንረካ ይሆናል። ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ እንዳን ለውጥና ወደ ተሻለ እንዳናመራ ጭንቅላታችን ይጋረዳል። ይህ ሁኔታ ሜታፊዚክሳዊ ይባላል። ሌላው ቆልፎን የሚይዘው ተጨባጭ የፖለቲካና የህብረተሰብ አወቃቀር ጉዳይ ነው። አንድ የተበላሸ ስርዓት ካለ እጃችንን ቆልፎ ይይዘናል። አላላውስ ይለናል። የሚሆን የማይሆን ነገር እየተከተለና ተግባራዊ እያደረገ የኑሮን ትርጉም እንዳንረዳ ያደርጋል። ዛሬ በአገራችንም ሆነ በብዙ የሶስተኛው ዓለም አገሮች የሚታየው ሁኔታ ይህ ነው። የኔ እመቤት የኛ ህይወት ፣ የኑሮ ትርጉም በኛ መደንገጉን ካቆመ ከርሞአል። ከውጭ ሆነው በሪሞት ኮንትሮል የሚቆጣጠሩን አሉ። ምን መብላት እንዳለብን ፣ እንዴት እንደምንኖር ፣ ምን ዐይነት መንግስትና ስራዓት እንደሚያሰፈልግን እኛው ወሳኞች መሆን ሲገባን ከውጭ ይወሰንልናል። ያለውን ደካማ ጎናችንን ተገን አድርገው እንደፈለጉ ያሽከርክሩናል። ይጠመዝዙናል። እነዚህ ኃይሎች እኛ በሰላም ወይም በጦር መኖር እንዳለብን የሚወስኑ ዓለምን የሚቆጣጠሩ ናቸው። የዓለም ህዝብ በጥቂት ኃይሎችና በአፈ ቀላጤዎቻቸው ፍዳውን እያየች ነው።*

*እዚህ ላይ ሴት ልጄ ያለችን ላጨውትሽ። በ*2006 *ዓ.ም ዩኒቨርሲቲ ከመግባቷ በፊት ለሰራ ልምምድ በበጋው ወር ለሶስት ወር ያህል አሜሪካ ትሄዳለች። ከዚያ ስትመለስ ዩኒቨርሲቲ መግባት ስለነበረባት የመመዝገቢያው ጊዜ ስላለፈ ከጀርመን ውጭ እንልካታልን። እያቅማማች ትሄዳለች። ትምህርቱን ቀጥላ አንድ አራት ወር ከተከታተለች በኋላ ስለትምህርቱ ሁኔታና አሰጣጥ እጠይቃታለሁ። በጣም ጥሩ እንደሆነና ደስ እንዳላትም ካጫወተኝ በኋላ የሚገርመው ነገር አለችኝ። ምነው ስላት! የሰው ለጅ ደደብ እየሆነ ነው የመጣው። ሁሉን ነገር የግሪክ ፈላስፋዎች አዘጋጅተው ሄደዋል። እነዚህ ሰዎች በጣም ብልህ መሆን አለባቸው ብላ ነገረችኝ። የምትከታተለውም ይህንን ስለሆነ ነገሩን ልትገነዘብ ችላለች። ይህንን ለአንድ የጀርመን የፍልስፍና ምሁር ጓደኛዬ ለሆነው አጫውተዋለሁ። በጣም ጥሩ ግንዛቤ ነው ብሎ መለሰልኝ። አየሽ የኔ እመቤት የምን መራበት ፍልስፍና የተበላሸ ስለሆነ መንገዱ ሁሉ ጨልሞብናል። የኑሮ ትርጉሙንን እንዳን ረዳ ሆነናል። ስለዚህም ሀቀኛውን መንገድ መከተል ወደ ገደል ከመግባት ያድነናል።*

***<u>ዘነበች</u>*** *፣ ፈቃዱ ለሰጠኸኝ ትምህርታዊ መልስ ምስጋናዬ ይድረሰህ። አንድ የመጨረሻ ጥያቄ ልጥይቀህ። ብዙ ቁም ነገሮችን ተወያይተናል። አየህ እኛ እስክንፈላሰፍ ድረስ ብዙ ጊዜ ሊፈጅ ነው። የጠማው ፣ የተራበ ፣የተጎሳቆለ ህዝብ ደግሞ እንዳንተ ያሉ ሲራቀቁብት ሊጠብቅ አይችልም። የአገራችንም ሁኔታ በዚህ ሊቀጥል አይችልም። ከዚህ ወዲያ ሌላ የሞት ሞት የለም። አየህ አንደ እፍኝ የማይሞሉ ሰዎች ሰባሰባት ሚሊዮን ህዝብ እያዋከቡና እንደከብት እየነዱ መኖር ይለባቸውም። ይገድላለ። ያስራሉ። ያሰቃያሉ። እንዳይሰራ ያደርጋሉ። ታዲያ ይህ ህዝብ ዝም ብሎ ማየት አለበት ? እስከ መቼ ነው ተዋርዶ የሚኖረው ? የመጣው ይምጣ ብሎ ለምን አንድ ጊዜ አይነሳም? ከዚህስ በኋላ ምን ሊመጣ ነው ?*

__ፈቃዱ__ ፤ አየሽ ዘነበች ፖለቲካ በስሜት የሚሆን ነገር አይደለም። ትግስትን ይጠይቃል። ጥበብንና ስልትን ይጠይቃል። እያንዳንዱ ነገር የራሱ ህግ አለው። ልጅ ሳይፀነስ አይረገዝም። ሳይረገዝም አይወለድም። ከተወለደም በኋላ ራሱን ለመቻል ብዙ ጠመዝማዛ መንገዶች ማለፍ አለበት። ህብረተሰብም እንደዚህ ነው። የሰዎች አስተሳሰብ የተለያየ እንደመሆኑ መጠን በመማርና በማስተማር ራጋ እያሉ መጓዝ ያስፈልጋል። በተለይም ለእንደኛ ያለው ህብረተሰብ ፤ ሁሉ ነገር በእልክ በሚካሄድበት አገር የተቃዋሚው ኃይል የገዢውን መደብ ሲቪል በሆነ መልክ መቅረብ አለበት። ማባበልና ማሻሸት አለብት። እንደልጅ ማለት ነው። ተቃወሚውም በልክ የሚነሳ ከሆነ ወደ መጠፋፋት ያመራል። ስለዚህ አረማመዳችን ከበርቴያዊ ፖለቲካን ያካተተ መሆን አለበት። ለወደፊቱ አብሮ የሚያኖረንን ከአሁኑ መቀየስ አለብን። በአቋም ብንለያይም ተቻችለን የምንኖርበት ፤ ተሰዳድበንና ተጨቃጭቀን አንድ ላይ ተቀምጥን ጠጅ የምንጠጣበትና ምግብ የምንበላበትን ሁኔታ መፍጠር አለብን። ፍቅርን ማሰተማር አልብን። ካለበለዚያ ትግላችን ሁሉ የአጭር ጉዞ ዐይነት ይመስላል። በአጭሩ ይቀጫል። ስለዚህ የገዢውን መደብ እንዲሰለጥን ረጋ ብለን መቅረብ አለብን። ባህል እንዲኖረው መንገዱን ማሳየት አለብን። ጥሩ መሰረት የሚኖረው ቤት ለመስራት የምንፈልግ ከሆነ እንደዚህ ነው መራመድ ያለበን። የኔ እህት የኔ መልስ ይህ ነው። በዕውነቱ ጊዜሽን ወስደሽ ለጥያቄዎቼ መልስ በመስጠትሽም ሆነ እኔንም መልሰሽ በመጠየቅሽ ትልቅ ምስጋና አቀርብልሻለሁ። በጣም ብዙ ወሬ አጫወትሽኝ።

__ዘነበች__ ፤ እኔም አመሰግናለሁ። በጣም ደስ የሚልና ትምህርት ያዘለ ውይይት ነው። ቀጥልብት

**አቀነባባሪ**

## ፈቃዱ በቀለ / ከበርሊን